አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች

በ

ቤተልሔም መብራቴ አየለ

ሐምሌ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ


በ

ቤተልሔም መብራቴ አየለ

አማካሪ

ሰላማዊት መካ (ረዳት ፕሮፌሰር)


2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች

በ


ቤተልሔም መብራቴ አየለ


ሐምሌ 2016 ዓ.ም

## የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም፡- ሰላማዊት መካ (ረዳት ፕሮፌሰር) ፊርማ፡- ...........

የውስጥ ፈታኝ ስም፡- -------------------------- ፊርማ፡- ...........

የውጭ ፈታኝ ስም፡- ------------------------------- ፊርማ፡- ...........

# ምስጋና

ጥናቱ ይህን ቅርጽ እንዲይዝ በማማከር እና በማስተካከል ከፍተኛ እገዛ ያደረገኝልኝን አማካሪዬ ሰላማዊት መካ (ረዳት ፕሮፌሰር) በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡

በተጨማሪም ለጥናቱ አስፈላጊመረጃዎችን የሰጡኝን ሰላማዊት አበራ፣ ወንድሜ ዮናስ መብራቴ፣ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር እንዲሁም በከፍተኛ ቅንነት ጥናቱን በማረምና መዋቅሩን በማስተካከል ድጋፍህ ያልተለየኝን ዮሐንስ ደርበው ጉባይን አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና ........ i

ማውጫ ........ ii

አጠቃሎ ........ iv

ምዕራፍ አንድ ........ 1

1. መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 3

1.4. የምርምር ጥያቄዎች ........ 3

1.5. የጥናቱ ዘዴ ........ 3

1.6. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 5

1.7. የትንተና ዘዴ ........ 6

1.8. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 6

1.9. የጥናቱ ወሰን ........ 6

ምዕራፍ ሁለት ........ 7

2. ክለሳ ድርሳን ........ 7

2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ........ 7

2.1.1. እንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ ........ 7

2.1.2. የእንስት አካል መፈረጃ ........ 9

2.1.3. የአካል ርዕዮት ........ 10

2.2. የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ........ 11

ምዕራፍ ሶስት ........ 14

3. የመረጃ ትንተና ........ 14

3.1. ከ2010 እስከ 2012 በታተሙ የዘፈን አልበሞች ውስጥ የሴት ውስጣዊ ገጽታ ........ 14

3.2. ከ2010 እስከ 2012 በታተሙ የዘፈን አልበሞች ውስጥ የሴት ውጫዊ (አካላዊ) ውበት ........ 24

ምዕራፍ አራት ........ 35

4. ማጠቃለያ ........ 35

4.1. ማጠቃለያ ........ 35

ሀ. ቀዳማይ የመረጃ መምንጮ ........ 38

ለ. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ........ 39

አባሪ ........ 40

# *አጠቃሎ*

*ይህ ጥናት “ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች” በሚል ርዕስ የተካሄደ ሲሆን፤ዋና ዓላማውም በተጠቀሰው ዘመን ሴትነት እንዴት እንደተሳለ በእንስታዊያን የሥነ-ጽሑፍ ሂስ የይዘት ትንተና ማድረግ ነው። በንድፈ ሐሳቡ መተገኒያነት  በግጥሞቹ ውስጥ የሴት አቀራረጽ፣ ውስጣዊ እና ውጫዊ (አካላዊ) ውበት እንዴት እንደተሳለ ተመርምሯል። በዚህም ሴቶች ከማኅበረ ባህሉ ውጪ በራሳቸው መንገድ በመንዛቸው መኮነናቸው፣ ውበታቸው በተለምዷዊው የውበት ማወደሻ መቅረቡ፣ ቅንድብ፣ ከንፈር እና ዐይን ወንድን የሚስቡ የቆንጆ ሴት ማሳያ ሆነዋል። ከውስጣዊ ውበት አንጻርም ሴቶች የሰናይ ባህሪ ባለቤት ተደርገው የሚገለጹት ማኅበረ ባህሉ ባዘጋጀላቸው መመዘኛ መሰረት መሆኑ፣ በብዙዎቹ ግጥሞች ሴቶች በማኅበረ ባህሉ መለኪያት ተመዝነው አታላይ፣ ከሃዲ፣ ተገዢ ተደርገው የተሳሉበት እና በራሳቸው አዲስ ማንነት የሚሄዱ ከአባታዊው ዓለም ልማድ ቀድመው የወጡ ሴቶች ተመልሰው የልማድ እስረኛ መሆናቸው ጥሩ ሰበዕና ሲያስብላቸው ታይቷል።*

*በአጠቃላይ በወንዶች ስለ ሴቶች የሚገጠሙ ግጥሞች የአባታዊውን ስርዓት የሚያንጸባርቁ ሆነው ተገኝተዋል። እንስቶች ለወንዶች ደስታ እና ግዞት በሚመች መልኩ ተስለዋል። የወንዶች ብዕር ብዙውን ጊዜ እንስታዊነትን የሚገልጸው አባታዊው ዓለም በሚፈልገው ሁኔታ ብቻ ሆኗል። ተተኳሪ ግጥሞቹ የቀረቡበት ይዘት ሴትን ዝቅ አድርጓል። በእንስታዊው የሥነ-ጽሑፍ ሂስ ዐይን መረዳትም አብዛኞቹ ግጥሞች ሴቶችን ያቀረቡበት ሁኔታ “የተዛባ’ የሚያስብል መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።*

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

በሀገራችን የዘፈን ግጥሞች ባህርያትን የተመለከተ በመረጃ የተደገፈ በቂ ጥናት የለም፡፡ ይህን አስመልክቶ ውቤ ካሳዬ ለሁለተኛ ዲግሪ ባቀረበው የመመረቂያ ጽሑፍ "ኢትዮጵያ ዓለማዊ ዘፈን መቼ እንደተጀመረ ለማወቅ ያስቸግራል፤ እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ የዘፈን ግጥሞችን በተመለከተ በአጥጋቢ ሁኔታ የተጻፈ የለም" (Wube፣26) ሲል ገልጿል፡፡ አሸናፊ ከበደ በ1971 ዓ.ም ካቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ በመነሳትም በሀገራችን የሚገኙ የዘፈን ዓይነቶች (class/type) ናቸው የሚላቸውን ለይቶ÷ ዘፈን፣ እንጉርጉሮ፣ ሽለላ፣ ለቅሶ፣ የበዓላት ዘፈኖች፣ የሰርግ ዘፈኖች፣ ምስጋና፣ መዝሙር፣ ዘመናዊ ዜማ እና ፖለቲካዊ መዝሙሮች መሆናቸውን ዘርዝሯል፡፡

ይሁን እንጂ የአማርኛ ዘፈኖችን ከላይ በተዘረዘሩት ዓይነቶች ለመከፋፈል ቢሞከርም ክፍፍሉ የተካሄደው በአብዛኛው ጥንታዊውን ባህላዊ የዘፈን ዓይነቶች እንጂ ዘመናዊ ግጥምን መሰረት በማድረግ ስላልሆነ በአሁኑ ወቅት በካሴት እየታተሙ የሚወጡ ዘፈኖችን ለማካተት አያስችልም፡፡ ከዚህ የምንረዳውም በጥናቱ ተለይተው በዓይነት ሊመደቡ ያልቻሉ ዘፈኖች ሊኖሩ መቻላቸውን ነው፡፡ ስለዚህ የዘፈን ግጥምን በተመለከተ በሀገር ውስጥ በቂ መረጃ ባለመገኘቱ የሌሎች ሀገሮችን ብያኔ መመልከት ይገባል፡፡

እንደሚታወቀው ከሥነ-ግጥም ዘርፎች አንዱ የዘፈን ግጥም (Lyrics) ሲሆን ሌሎቹ ትረካ እና ተውኔታዊ ናቸው፡፡ በጥንታዊ ግሪክ የዘፈን ግጥም በሙዚቃ መሣሪያ በተለይም በክራር እያጀቡ ማቅረብ የተለመደ ነበር፡፡ ሌሪክ የሚለው ቃልም ግሪኮች “ሊኖራ” ከሚሉት የሙዚቃ መሣሪያ እንደተገኘ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የዘፈን ግጥም በውስጥ የሚብላላን ረቂቅ ስሜት ምስልና ቅርጽ ሰጥቶ የሚያሳይ በመሆኑ፤ ከገጸ ባህሪው ድርጊት ይልቅ ለአድማጭ በቀጥታ የውስጣዊ ስሜትን ሁኔታ እና አስተሳሰብ ለመግለጽ ብሎም ስሜቱን ለአድማጭ ሊያሻግረው በሚፈለገው ጉዳይ ተመርኩዞ ይደረሳል፡፡

የዘፈን ግጥም ጾታዊ ፍቅርን፣ ጦርነትን፣ ሰላምን፣ ማግኘትን፣ ማጣትን ወዘተ ጭብጡ አድርጎ ስለሚደረስ እንደ ገጣሚው ፍላጎትና እንደተጻፈበት የዘመን መንፈስ የተለያየ ቀለም ይይዛል፡፡

የዘመን መንፈስ ደግሞቀለሙን ከሚቀያይርባቸው  ሁኔታዎች አንዱ በየጊዜው የሚኖረው የርዕዮተ ዓለም መለዋወጥ በመሆኑ በዚህ ጥናት እንደ ማሳያ ሆኖ የቀረበው የእንስታዊነት

የርዕዩተ ዓለም የዘፈን ግጥሞችን ሁኔታ በራሱ መንገድ በመቀያየር የጊዜውን ሁኔታ እንዴት ሊያሳይ እንደሚችል ለማሳየት ይሞከራል፡፡

እንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ በሥነ-ጽሑፍ ሥራ ውስጥ አዲስ ገጽታን ማግኘት የሚያስችል መተንተኛ ሲሆን÷ አዳዲስ ጥያቄዎችን በመጠየቅም ምላሽ ያቀርባል፡፡ መሰረታዊ ጉዳዩም ማኅበረሰቡ ለሴቶችና ወንዶች የሰጠውን የማኅበረ ባህላዊ ደረጃ ልዩነት ማወቅ፣ የልዩነቱን አንድምታ መመርመር እንዲሁም ለልዩነቱ መፈጠር ምክንያትና ውጤቱን ማሳየት ነው፡፡

በዚህ ጥናትም በእንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ ማብለያነት የተመረጡ የዘፈን ግጥሞች ተተንትነው በርካታ ትርጓሜዎችን ይዘው ቀርበዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት "ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው፡፡ በጊዜ ረገድ ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም ከታተሙ አልበሞች ውስጥ በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች ላይ ሴቶች ከውስጣዊ ገጽታ እና ውጫው (አካላዊ) መልክ አኳያ እንዴት እንደተሳሉ የይዘት ትንተና ማድረግ ነው፡፡

በጥናቱ በሚያቅፈው ዘመን ውስጥ ሴትነት ከማህበረ ባህሉ እና መህበረባህሉ ከፈጠራት ውጪ በራሳቸው መንገድ በመጓዛቸው እና ከአባዎው ስርዓት ውጪ በመኖራቸው በግጥም ውስት በወንዱ እንዴት እንደተተረኩ ተተንትኗል፡፡ የተመረጡት የዘፈን ግጥሞች ሲጠኑ፣ የእንስታዊነት ስነ ጽሁፍ ንድፍ ሐሳብ፣ ዕይታዎች እነዚህን ምንትነቶች በአዲስ መልክ ለመመዘን ያግዛሉ፡፡ ስለሆነም ግጥሞቸትን ከእንስታዊነት አቅጣጫዎች መመርመር መልካሙን የነገረ ጾታ አስተማስሎ ለማበረታታትና አሉታውን ለመቅረፍ የራሱ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጥናቱን ለማካሄድ ካነሳሱ ምክንያቶች የመጀመሪያው በተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ (በልቦለድ፣ በአጭር ልቦለድ) ላይ ሴትነት የመፈተሹን ያህል በዘፈን ግጥሞች ላይ አለመጠናቱ ነው፡፡

ሁለተኛው የዘፈን ግጥሞችን በመተንተን ትርጓሜዎች እንዲኖሩት የሚያስችል የሃያሲ ዐይን ሊኖር ስለሚገባ በዘመኑ የዘፈን ግጥም ውስጥ ጎልተው የወጡ ርዕሰ ጉዳዮችን በእንስታዊ የሥነ-ጽሑፍ ሂስ መግለጥ ስለተፈለገ ነው፡፡ በቤተ-መጻሕፍት እና በይነመረብ ላይ ባደረግሁት የሥነ-ጽሑፍ ሂስ ጎሠሣ የዘፈን ግጥምን ጉዳያቸው አድርገው ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ

የተሠሩ  ዘጠኝ ጥናታዊ ጽሑፎችን አግኝቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቶቹ በወንድ ገጣሚያን የሚቀረጹ ሴቶችን፣ ውስጣዊ ገጽታ እና ውጫዊ (አካል)ምልክ አላሳዩም፡፡ ስለሆነም ይህን ክፍተት ለመሙላት ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ጥናቱን ለማካሄድ ተነስቻለሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የእዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም በታተሙ አልበሞች ውስጥ ወንዶች በደረሷቸው የዘፈን ግጥሞች ላይ ሴቶች ከውስጣዊ ገጽታ እና ውጫዊ (አካላዊ) መልክ አኳያ የቀረቡበትን ሁኔታ በእንስታዊያን ንድፈ ሐሳብ አንጥሮ ማሳየት ነው፡፡

### ዝርዝር ዓላማዎች

- ወንድ የዘፈን ግጥም ደራሲዎች ሴትን ልጅ የሚቀርጹበትን መንገድ ማመላከት፤
- በግጥሞቹ ውስጥ የሴት ሰናይ እና እኩይ ምግርባን ማሳየት፤
- በተለያዩ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ስለ ሴት ተደጋግሞ ምን እንደተነሳ መጠቆም የሚሉት የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ናቸው፡፡

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ በዋናነት ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም በታተሙ አልበሞች የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ሴትነት እንዴት ቀረበ? የሚለውን ዐቢይ የምርምር ጥያቄ ጥናቱ ይመልሳል፡፡ በተጨማሪም በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ የሴት ልጅ ውስጣዊ ገጽታ ምንድን ነው?፣ የሴት ልጅ ውጫዊ (አካላዊ) መልክስ) እንዴት ተገለጸ?፣ የሴት ልጅ ጥሩ ሰብዕና ምንድን ነው?፣ በተመረጡ የዘፈን ግጥም ናሙናዎች ውስጥ ስለሴት ተደጋግሞ የቀረበው ጉዳይስ ምንድን ነው? የሚሉትን ዝርዝር ጥያቄዎችይመልሳል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

የተተነተኑየዘፈን ግጥሞች የተመረጡት በዓላማ ተኮር የናሙና መምረጫ ዘዴ ነው፡፡ዘዴው የተመረጠውም የጥናቱን ዓላማ ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን በቀጥታ የመምረጥ መብትስለሚሰጥ ነው፡፡ለአስረጅነት በተመረጠው ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ኤጀሲ፣ በኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር፣ ከሙዚቃ አሳታሚዎች፣ ከበይነ መረብ እና ከተለያዩ የሙዚቃ ምርት ሻጭ ግለሰቦች ባደረግሁት ተደጋጋሚ ፍለጋ ሃያ ስምንት አልበሞችን አግኝቻለሁ፡፡

እነዚህን አልበሞች ከበይነ መረብ፣ ከኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር፣ ከሙዚቃ አሳታሚዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ ባደረግሁት ፍለጋ ያገኘኋቸው እንጅ፤ ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም ባለው ጊዜ የታተሙት የዘፈን አልበሞች እነዚህ ብቻ ናቸው የሚል መደምደሚያ የለኝም፡፡ ምክንያቱም በተለያየ ቦታ፣ሁኔታ እና ግለሰቦች ስለሚታተሙ እንዲሁም በአንድ ቋት ተሰብስበው የማይገኙበት ሁኔታ ስላለ ነው፡፡

ስለሆነም ከሃያ ስምንቱ አልበሞች ውስጥ የተተኳሪ ግጥም ደራሲዎች ግጥም የተካተቱባቸው ስድስት አልበሞች በታላሚ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ከእያንዳንዳቸው አልበሞች ሁለት ሁለት ዘፈኖች ተመርጠው ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

እነሱም፡- ብስራት ሱራፌል በ2010 ካሳተመው ‹‹ቃል በቃል›› ከሚለው አልበም ውስጥ የሶሎሞን አምባው ድርሰት የሆነው ‹‹ወይንዬ›› እና የናትናኤል ግርማቸው ድርሰት የሆነው ‹‹እይዋት››፣ ቴዎድሮስ ካሳሁን በ2010 ካሳተመው ‹‹ኢትዮጵያ›› ከሚለው አልበም ውስጥ የቴዎድሮስ ካሳሁን ድርሰት የሆኑት ‹‹መማጸኔ›› እና ‹‹ያምራል››፣ እሱባለው ይታየው በ2010 ካሳተመው ‹‹ትርታዬ›› አልበም ውስጥ የእሱባለው ይታየው ድርሰት የሆኑት ‹‹ማሬ ማሬ›› እና ‹‹ሳምናት››፣ ዳዊት ጽጌ በ2012 ካሳተመው ‹‹የኔ ዜማ›› አልበም ውስጥ የአበበ ብርሃኔ እና የናትናኤል ጌታቸው የጋራ ድርሰት የሆነው ‹‹ደሣለኝ›› እና የቴዎድሮስ ካሳሁን ግጥም የሆነው ‹‹ባየው ባየው››፣ ጎሳዬ ቀለሙ በ2011 ካሳተመው ‹‹ባላምባራስ›› አልበም ውስጥ የቢኒያም እሸቱ እና የፀጋው ተክሉ የጋራ ድርሰት የሆነው ‹‹ቀዳማዊት›› እና የቢኒያም መስፍን እና ኤሊያስ ግዛቸው የጋራ ድርሰት የሆነው ‹‹ኖረሻል እንዴ››፣ ጎሳዬ ተስፋዬ በ2012 ካሳተመው ‹‹ሲያምሽ ያመኛል›› አልበም ውስጥ የዓለማየሁ ደመቀ ድርሰት የሆነው ‹‹ከእሁድ እስከ እሁድ›› እና የጎሳዬ ተስፋዬ ድርሰት የሆነው ‹‹ተረጋጋሽ ወይ›› የሚሉት ናቸው፡፡

ጊዜው የተመረጠው በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የታዩ ለውጦችን ተከትሎ በኢትዮጵያ ታሪክ በከፍተኛ ኃላፊነት ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 50 በመቶ የሆነበት መሆኑ እና ይህም ከእንስታዊያን ርዕዮት አንጻር ጎሊናዊ ንቃትን የሚፈጥር ስለሆነ በዘፈን ግጥሞች ውስጥ የቀረበበትን ሁኔታ መመርመር በማስፈለጉ ነው፡፡

## 1.6. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ከኢትዮጵያ ብሔራዊቤተ-መጻሕፍትእና ቤተ-መዛግብት፣ ከኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር፣ ከሙዚቃአሳታሚዎች፣ ከበይነ-መረብ እና ከተለያዩ የሙዚቃ ምርት ሽጭ አካላት ባደረግሁት ተደጋጋሚ ፍለጋ 28 አልበሞችን አግኝቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ አልበሞች በተለያየ ቦታ፣ሁኔታ እና ግለሰብ ስለሚታተሙ እንዲሁም በአንድ ቋትተሰብስበው የማይገኙበት ሁኔታ ስላለ ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም የታተሙት የዘፈን አልበሞች ያገኘኋቸው ብቻ ናቸው የሚል መደምደሚያ የለኝም፡፡

ከ28 አልበሞች መካከል ከጥናቱ ዓላማ ጋር ባላቸው ቁርኝት መሠረት ሥድስት አልበሞች፤ ከእያንዳንዱ አልበምም ሁለት የዘፈን ግጥሞች በታላሚ ናሙና ዘዴተመርጠው ተተንትነዋል፡፡

የተመረጡት አልበሞችና የዘፈን ግጥሞችም÷ ብስራት ሱራፌል በ2010 ከአሳተመው ‹‹ቃል በቃል›› አልበም ውስጥ የሶሎሞን አምባው ግጥም ‹‹ወይንዬ›› እና የናትናኤል ግርማቸው ‹‹እይዋት››፣ ቴዎድሮስ ካሳሁን በ2010 ከአሳተመው ‹‹ኢትዮጵያ›› አልበም ውስጥ የራሱ የዘፋኙ ድርሰቶች ‹‹መማጸኔ›› እና ‹‹ያምራል››፣ እሱባለው ይታየው በ2010 ከአሳተመው ‹‹ትርታዬ›› አልበም ራሱ የደረሳቸው ‹‹ማሬ ማሬ›› እና ‹‹ሳምናት››፣ ዳዊት ጽጌ በ2012 ከአሳተመው ‹‹የኔ ዜማ›› አልበም ውስጥ የአበበ ብርሃኔ እና የናትናኤል ጌታቸው የጋራ ድርሰት ‹‹ደሣለኝ›› እና የቴዎድሮስ ካሳሁን ግጥም የሆነው ‹‹ባየው ባየው››፣ ጎሳዬ ቀለሙ በ2011 ከአሳተመው ‹‹ባላምባራስ›› አልበም ውስጥ የቢኒያም እሸቱ እና የፀጋው ተክሉ የጋራ ድርሰት የሆነው ‹‹ቀዳማዊት›› እና የቢኒያም መስፍን እና ኤሊያስ ግዛቸው የጋራ ድርሰት‹‹ኖረሻል እንዴ››፣ ጎሳዬ ተስፋዬ በ2012 ከአሳተመው ‹‹ሲያምሽ ያመኛል›› አልበም ውስጥ የዓለማየሁ ደመቀ ድርሰት ‹‹ከእሁድ እስከ እሁድ›› እና የጎሳዬ ተስፋዬ ድርሰት የሆነው ‹‹ተረጋጋሽ ወይ›› ናቸው፡፡

በተለያየ ጊዜ በዘፈን ግጥሞች ላይ ጥናቶች ቢካሄዱም÷ የአብዛኞቹ ትኩረት የግጥሞቹ ቅርጽ እና ይዘት ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ በመሆኑም በዘፈን ግጥሞች ውስጥ ሴትነትን ጉዳዩ አድርጎ የመረመረ ጥናት ስላላጋጠመኝ ይህንኑ ክፍተት ለመሙላትየእኔ ጥናት “ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች” በሚል ርዕስ ተካሂዷል፡፡

የእዚህ ጥናት የዘፈን ግጥሞች ከሙዚቃ ቤቶች በግዥ እንዲሁም ከበይነ-መረብ ተሰብስበዋል፡፡

ቀዳማይ እና ዳኅራይ የመረጃ ምንጮች አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን፥ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ተጠኝ የዘፈን ግጥሞች፤ ዳኅራይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ የጥናቱን ዓላማ ዳር ለማድረስ የሚቀርቡ ሐሳቦችን የሚደግፉ ጽሑፎች ናቸው፡፡

## 1.7. የትንተና ዘዴ

ተመረጡ የዘፈን ግጥሞችን ይዘት መተንተን የጥናቱ ትኩረት ነው፡፡ በታላሚ የናሙና ዘዴ በተመረጡ ተተኳሪ የዘፈን ግጥሞች ውስጥም የሴት ውስጣዊ ገጽታ እና ውጫዊ (አካላዊ) መልክ አቀራረጽን ለመመርምር እንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

## 1.8. የጥናቱ አስፈላጊነት

የዘፈን ግጥም ለተዝናኖት፣ ለገቢ፣ ለማስተማሪያ፣ በውስጥ የሚብላላን ስሜት ለመተንፈስ እና ለሌሎች ፍላጎቶች ይጻፋል፡፡ በይዘቱም በቀላሉ ተዝናኖትን ከመፍጠር እስከ ጠንካራ መልዕክቶች ሊቀርቡበት ይችላሉ፡፡ በዚህም ውስጣዊ ውበትን፣ ውጫዊ (አካላዊ) ውበትን፣ ፍቅርን፣ ጥላቻን፣ በቀልን፣ ማግኘትና ማጣትን ጨምሮ ሌሎች በገጣሚው ውስጥ የሚንሸራሸሩ ጉዳዮች በግጥሞቹ ውስጥ ይነሳሉ፡፡

ይህ ጥናት በሚያካልላቸው ዘመናት በታተሙ የዘፈን አልበሞች ግጥሞች ውስጥም ሴት ልጅ የተገለጸችበትን ሁኔታ ተንትኖ በማቅረብ ወንድ ገጣሚዎች ለሴቶች ያላቸውን መረዳት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም በጉዳዩ ላይ ጥናት እንዲካሄድ መነሳሳትን በመፍጠር እና ለአጥኝዎች መረጃ በመስጠት ይጠቅማል፡፡

## 1.9. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከጊዜ አንጻር ከ2010 እስከ 2012 ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ሲሆን በዚሁ ዘመን ታትመው ካገኘኋቸው 28 አልበሞች መካከል በታላሚ ንሞና በተመረጡ ሥድስት አልበሞች ላይ ተገድቧል፡፡ ከእያንዳንዱአልበሞችም ሁለት በድምሩ 12 የዘፈን ግጥሞችን ይዘት በመተንተን ላይተወስኗል፡፡ እንዲሁም ከዘፈን ግጥም ደራሲዎች አኳያ በወንዶች ብቻ በተደረሱት ተወስኗል፡፡ ይህ የሆነውም (በሴት የዘፈን ግጥም ደራስያን የተደረሱት ያልተካተቱት) የጥናቱ ትኩረት ወንድ ገጣሚዎች ሴትነትን የሚረዱበትን እና የሚቀርጹበትን ሁኔታ ተንትኖ ማሳየት በመሆኑ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል የጥናቱ መሠረታዊ ጉዳይ የሆነው የእንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ የሚቃኝ ሲሆን በቀጣዩ ክፍል ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ይቀርባሉ፡፡

### 2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

#### 2.1.1. እንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ

ሥነ-ጽሑፍ እንደሙያ መጠናት ከጀመረ አንስቶ የሥነ-ጽሑፍ ማጥኛ ንድፈ ሐሳቦች በየጊዜው ተቀምረዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የቅርብ ጊዜ ንድፈ ሐሳብ እንደሆነ የሚታመንበት እንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ አንዱ ነው፡፡ ሥነ-ጽሑፍን በእንስታዊነት መነጽር መመልከት በ1960ዎቹ መጀመሪያ መጎልበት ጀምሮ በ1980ዎቹ ወደ ጽንሰ ሐሳብ ደረጃ ማደጉ ይታማናል፡፡

የእንስታዊነት እሳቤ በጾታዎች እኩልነት ላይ ከሴቶች መብት ጋር የተያያዘ ሲሆን የሴቶችን መብት እና ጥቅሞች በመወከል በተደራጀ እንቅስቃሴ በጾታዎች መካከል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እኩልነት ላይ መሟገት ነው፡፡

የንድፈ ሐሳቡ ዋና ትኩረት በሕብረተሰቡ ውስጥ የጾታ እኩልነትን ማስረጽ ነው፡፡ ይህን ለማምጣትም እኩልነት ምንድን ነው? ለዚህ እኩልነት ተጠያቂው ማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ይሰነዝራል፡፡ ጥያቄውን ለመመለስም የመስኩ አቀንቃኞች ጥረትአድርገዋል፡፡ በዚህም ፈረንሳዊው ፈላስፋ ቻርለስ ፉሪየር ‹feminism› የሚለውንቃል በ1837 ከፈጠሩ በኋላ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ሂደቶች አልፎ አሁን እንስታዊነት ወደ ሚባለው ሥነ-ጽሑፋዊ ንድፈ ሐሳብ አድጓል፡፡

ስለ እንስታዊነት ንድፈ ሐሳብ ምንነት በየዘመኑ ከተሰጡ ብያኔዎች መካከል የሩት ፊኔጋን ሐሳብ ይጠቀሳል፡፡ በዚሁ ሐሳብ እንደተገለጸው እንስታዊነት አዳዲስ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ምላሹንም ይዞ የሚቀርብ ንድፈ ሐሳብ መሆኑ፤ መሰረታዊ ጉዳዩም ማኅበረሰቡ ለሴቶችና ለወንዶች የሰጠውን የማኅበረ ባህላዊ ደረጃ ልዩነት ማወቅ፣ የልዩነቱን አንድምታ መመርመር እና ለልዩነቱ መፈጠር ምክንያትና ውጤቱን ማሳየትና መረዳት መሆኑ ተብራርቷል፡፡

> Feminism is a method of analysis as well as a discovery of new materials. It asks new questions as well as coming up with new answers. Its central concern

is with the destination between men and women, with the fact of this distinction, with its meanings, and with it causes and consequences (Ruth, 5).

የእንስታዊያን አቀንቃኞች አባዊው የሥነ-ጽሑፍ ዓለም የቋንቋ ክምችት እንስቶችን ለወንዶች ደስታ እና ግዞት በሚመች ሁኔታ ነው ያዋቀረው በሚል ይቃወሙታል። እንስታዊነት የሚገለጸውም አባዊው ዓለም በሚፈልገው አካላዊና እና ሰብዕና ነው ይላሉ። ቋንቋ የጾታ ሚዛናዊነት ይጎድለዋል ተብሎ በሚሰበክበት ጊዜና ቦታ ያሉ ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎች ሚዛናቸው የተዛባ እንደሚሆንም ያነሳሉ።

Literature is a specific and irreducible from of discourse, but the language with constitutes the raw material of the text is the language of ideology, It is thus an inadequate of language, incomplete partial. Incapable of concealing the real contradictions' it is its purpose to efface. This language normally in flux, is arrested, 'congealed' by the literary text (Kowaleski, 603).

ሴቶች እምነታቸውን፣ አመለካካታቸውንና ስሜታቸውን የሚገልጹባቸው የኪነ ጥበብ ውጤቶች በወንዶች ሚዛን ተመዝነው ረብ የለሽ ሆነው ሲጣሉ እንደነበርም እንስታዊያኑ ይገልጻሉ። እንዲሁም ትክክለኛውን የሴቶች ምስል አዳምነው የሚቀርቡ የወንዶች የፈጠራ ሥራዎች ተቀባይነት ማግኘታቸውንና ኪነ-ጥበባዊ ውበት የተላበሱ ናቸው ተብለው መወደሳቸውን ይቃወማሉ።

One of the first phase of feminist literary criticism involved examining male authored text for accurate or biased and faulty depiction of female experience. Another task of feminist literary criticism has been the recovery of "lost" neglected works by female authors (Kolwleski, 385).

ከእንስታዊ የሥነ-ጽሑፍ ሂስ ትኩረቶች አንዱ በወንዶች የተጻፉ ሥራዎች የሴቶችን ኑሮ በትክክል ወይም በተዛባ ሁኔታ ማቅረባቸውን መመርመር ነው። በዚህም በአባዊው የሥነ-ጽሑፍ ርዕዮት ተቃኝተው የወጡ የወንዶች የፈጠራ ሥራዎች ስለሚዛናዊነታቸው ወይም ስለ አድሎአዊነታቸው በእንስታዊያኑ አንጻር ትንታኔ እንዲቀርብበት ያተጋል።

የእንስታዊነት የሥነ-ጽሑፍ ሂስ ተግባር አንድም ጽሑፋዊ እና ቃላዊ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች ቀድሞ ባልታዩበት አዲስ አንጻር ተመልክቶ ትርጓሜ መስጠት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ስለ

ሴቶች የሕይወት ተሞክሮ የሚያወሱ የፈጠራ ሥራዎች አድሎአዊ ምስል ማመልከት ወይም አለማመልከታቸውን ማሄስ ነው፡፡

እንስታዊ የሥነ-ጽሑፍ ሂስ ማኅበረባህሉ ስለ እንስት የገነባውን ገጽታ በማፍስ እንስታዊ ማኅበረባህል እንዲሰፍን ማንቃት መሆኑን ኤልሳቤት ትገልጻለች፡፡ "It was in unique position critique notions to about women and literature, re examine the grounds of literary study. Recover non canonical women writers to establish a female literary history, and generates new insights in to the theory and practices of literary criticism" (Elizabeth, 164).

### 2.1.2. የእንስት አካል መፈረጃ

ወንዶች ባብዛኛው እንስቶችን ሲገልጹ ራሳቸው በሚያበጁት የተክለ-ሰውነት (አካላዊ) ፍረጃ ቆንጆ፣ መልከ-ጥፉ፣ አቅመ-ቢስ፣ ደካማ፣ ጠንካራ ወዘተ ይላሉ፡፡ ይህን ፍረጃ እንድትቀበልም ጫና ሲያሳድሩ ይስተዋላል፡፡ ማኅበረሰቡ ነሽ ከሚላት ውጭ መሆን እና መጠየቅም ተቀባይነቷን እንደሚያሳጣት ይጠበቃል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ አካሄድ በእንስታዊያን ንድፈ ሐሳብ አካሄድ ተገቢ እና ዘላቂ አለመሆኑን ጁዲት በትለር በአጽንኦት ትገልጻለች፡፡

> The body is also the situation of having to take up and interpret that set of received interpretations. No longer understood in its traditional philosophica lsenses of 'limit' or 'essence', the body is a field of interpretive possibilities, the locus of a dialectical process of interpreting anew a historical set of interpretations which have become imprinted in the flesh. The body becomes apeculiar nexus of culture and choice, and 'existing'one's body becomes a personal way of taking up and reinterpreting received gender norms. To the extent that gender norms function underthe aegis of social constraints, the reinterpretation of those norms through the proliferation and variation of corporeal styles becomes avery concrete and accessible way of politicizing personal life. (Butler, 45).

ተክለ ሰውነት ጾታን፤ ጾታም ተክለ ሰውነትን እንደማይገልጸው እና ጾታ የአካል አካልም የጾታ እስረኛ ሆኖ የሚቀጥልበት ልማድ  ብዙ ርቀት እንደማያስኬድ እንስታዊያኑ ያነሳሉ፡፡ ለዚህም

የማኅበረሰብ አመለካከት እና አስተሳሰብ በየጊዜው እንደሚቀያየረው ሁሉ ስለ የሴት ልጅ ውበት የሚቀርቡ መለኪያዎችም ወጥ እንዳልሆኑ ያስረዳሉ፡፡

በየዘመኑ ታትመው ለገበያ የቀረቡ ዘፈኖችን ግጥሞች ብንመረምር ከላይ የቀረበውን ሐሳብ ያጠናክራል፡፡ የሴቶችን አካል መሰረት አድርገው በወንዶች የሚገጠሙ ግጥሞች የዘመኑ እስረኛ እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ ልምሳሌ፡- ዳሌ፣ ባት፣ ወገብ፣ ተረከዝ፣ ጡት፣ ዐይን፣ ቁመት (ማጠር እና መርዘም)፣ ውፍረት፣ ቅጥነት ወዘተ. በየዘመኑ እየተፈራረቁ የሴት ልጅ የውበት መለኪያ ሆነዋል፡፡ በቀጣይም የተለያዩ ለውጦችን እንደሚያሳዩ የሚገመት ሲሆን፤ ለውጦቹ ግን የሴቷን ምንነት ተከትሎ ሳይሆን የማኅበረሰቡን ንቃት ተከትሎ ነው፡፡

### 2.1.3. የአካል ርዕዮት

በሴት ውስጥ የወንድ ማንነት በወንድ ውስጥ የሴት ማንነት ሊገኝ ይችላል በሚል እሳቤ መነሻነት አካልን በማየት ብቻ "ወንድ" ወይም "ሴት" ማለት እንደማያስማማ እንስታዊያን ይገልጻሉ፡፡

ሰው "ወንድ" ወይም "ሴት" ሆኖ እንደማይወለድ እና ጾታውን የሚተክለው ማኅበረሰቡ መሆኑ፤ ሁለት ዓይነት ጾታ እንዲኖር የተደረገውም ሕብረተሰቡ ውስጥ በሰረጸው ርዕዮት እንጂ ጾታ ሁለት ብቻ ስለሆነ አይደለም ሲሉም ያብራራሉ፡፡

ሴት ወይም ወንድ ተብሎ አካላዊ ሁኔታ በመመልከት የተሰጠ ውሳኔ ባህላዊ አተረጓጎም እና ተለምዷዊ አመለካከት መሆኑን በትለር ታስረዳለች፡፡

> That infants are divided into sexes at birth, Wittig points out, serves the social ends ofreproduction, but they might just as well be differentiated on the basis of ear lobe formation or, better still, not be differentiated on the basis of anatomy at all. In demarcating 'sex' as sex, we construct certain norms of differentiation. And in the interest which fuels this demarcationresides already a political program (Butler, 48).

በየቀኑ በሚደረጉ ድርጊቶች ውስጥ ሴትነት ውስጥ ወንድነት፣ ወንድነት ውስጥ ሴትነት አለ፤ ሴትን ሴት የሚያደርጋት ወንድን ወንድ የሚያደርገው በማኅበረሰቡ ባህል አስተምኅሮ እንጂ እውነት ወጥ የሆነ (አስማማጊ) እንዳልሆነም በትለር ትገልጻለች፡፡

ከላይ በቀረቡት የእንስታዊያን ንድፈ ሐሳብ ዕይታዎች መሠረት በዚህ ጥናት ወንድ የዘፈን ግጥም ደራሲዎች ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም ታትመው በወጡ የዘፈን አልበሞች ላይ ሴትን የቀረጹበት ሁኔታ ተመርምሯል፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት

ለውጭ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ አንድ እንዲሁም ለአማርኛ ቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ ቢ ኤ ዲግሪ ሟሟያ ሰባት ጥናቶች ቀደም ሲል ጉዳያቸውን የዘፈን ግጥም ላይ አድርገው ተካሂደዋል፡፡

ጥናቶቹ የዘፈን ግጥምን ይዘት ከቅርጽ ጋር አጣምረው ስላዩ፣ በወንድ ደራሲ የተደረሱ ግጥሞችን ብቻ ለይተው ስላላዩ፣ ሴት በወንድ ዘፈን ገጣሚ ዕይታ እንዴት ቀረበች ብለው ነጠላ ሰበዝ መዘው በርከት ያሉ አልበሞችን እና የዘፈን ግጥሞችን ባለማካለላቸው ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና የላቸውም፡፡

በመሆኑም ከእኔ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸውን ሁለት ጥናቶች በመምረጥ ቅኝት ተደርጓል፡፡ በእዚሁ መሠረት ሚካያ በኃይሉ ‹‹የውስጣዊ ሰብዕና አቀራረጽ በሶስና ታደሰ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ›› (1996) እና መላኩ ጌታቸው ‹‹በእጅጋየሁ ሽባባው የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ይዘት ትንተና (1998) የሚሉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ተዳስሰዋል፡፡

**ሚካያ በኃይሉ፡-** ‹‹የውስጣዊ ሰብዕና አቀራረጽ በሶስና ታደሰ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ›› በሚል ርዕስ በ1996 ዓ.ም ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ ዓላማዬ ብሎ የተነሣው በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ውስጣዊ ሰብዕናን መገምገም ነው (ገጽ 1)፡፡ ግምገማውም የሰው ልጅ ውስጣዊ ሰብዕና እንዴት እንደተሳለ እና ለሰብዕና አቀራረጽ ተጠቃሽ የሚሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮችን እንዲሁም በግጥሞቹ ውስጥ በተደጋጋሚ የተገለፁ የሰብዕና አይነቶችን መመርመር ነው፡፡

ዘዴውም ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥን የተከተለ ሲሆን፤ ወሰኑም በአንድ ነጠላ ጉዳይ (ውስጣዊ ሰብዕና) እና በአንዲት ገጣሚ ሥራዎች ብቻ ተገድቧል፡፡ በዚህም ከ1984 እስከ 1995 በወጡ የገጣሚዋ ግጥሞች ላይ ተመስርቶ፣ አሥራ ሦስት ግጥሞችን ተንትኗል፡፡

በአደረጃጀት ረገድም ይዘትን መሠረት አድርጎ የዘር ውርስ፣ ሕብረተሰብ ወይም አካባቢ (ቤተሰብ፣ የቤተሰብ የኑሮ አቅም፣ ሐይማኖት፣ ሚና)፣ አካላዊ አቋም፣ ሌሎች የሕይወት አጋጣሚዎች ተብሎ ቀርቧል፡፡

የሚካያ ጥናት በዘፈን ግጥም ላይ ተመስርቶ የይዘት ትንተና ማድረጉ እና ዓላማ ተኮር የአጠናን ዘዴን መከተሉ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በአንጻሩ በአንድ ገጣሚ መገደቧ፣ የሴት ገጣሚን ግጥም በመምረጧ እንዲሁም አንድ ነጠላ ጉዳይ (የሰብዕና አቀራረጽ) ብቻ በማየቷ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

የእኔ ጥናት ትኩረት ውስጣዊ ውበት እና ውጫዊ ውበትን (አካል) ይዘት መተንተን በመሆኑ፣ ስምንት ወንድ የዘፈን ግጥም ደራሲዎች የጻፏቸውን የዘፈን ግጥሞች በማየቱ፣ ከጊዜ አንጻርም የሚካያ ከ1984 እስከ 1995 የወጡ የዘፈን ግጥሞችን የእኔ ጥናት ደግሞ ከ2010 እስከ 2012 ያለውን አድማስ ማካለላችን ያለያዩናል፡፡

**መላኩ ጌታቸው፡-** ‹‹በእጅጋየሁ ሽባባው የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1998 ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡ በአጠቃላይ በዘፈን ግጥሞች የተሰሩ ጥናቶች አጥጋቢ አለመሆን እና የእጅጋየሁ ሽባባው ስራዎች አለመጠናታቸውም ጥናቱን ለማካሄድ እንዳነሳሳው ጠቅሷል፡፡ ዓላማውም እጅጋየሁ በዘፈን ግጥሞቿ ያነሳቻቸውን ጉዳዮች ይዘት መተንተን ሲሆን ገላጭ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡

በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝቱ ከእሱ ጥናት ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ጥናታዊ ስራዎች መጠቀሙ እና ጥናቱ የይዘት ትንተና ሲያድርግ ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ አለመጠቀሙ ጉድለቶች ናቸው፡፡

የመላኩም ሆነ እኔ ጥናት የዘፈን ግጥም ይዘት ትንተና ላይ በማተኮሩ መመሳሰል ቢኖርም በጥናቶቹ ከተካተቱ ግጥሞች መጠን፣ ዘፈኖቹ ከወጡበት ዘመን፣ ለማሳየት ከተፈለጉ ዓላማዎች እና በትንተና ማተኮሪያዎች ሰፊ ልዩነት አለ፡፡

የመላኩ ጥናት የተመረጡ ሰበዞችን መዝዞ ለሥነ-ጽሑፋዊ ፋይዳው ቦታ ሰጥ ከማቅረብ ይልቅ የዘፋኟን ስራ ይዘት መተንተን ላይ ሙሉ በሙሉ አተኩሯል፡፡ የእኔ ጥናት ወንዶች በሚጽፏቸው ግጥሞች ውስጥ ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ በእንስታዊ የሥነ-ጽሑፍ ሂስ በመመርመሩ መለያየት አለ፡፡በአብያተ መጻሕፍት እና በበይነ መረብ ላይ ባደረግሁት ኅሠሣ ልክ የዘፈን ግጥምን ጉዳያቸው አድርገው ዘጠኝ፤ አንድ የመዝሙር ግጥም ላይ ለቢኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተሠርተዋል፡፡ ሆኖም የዘፈን ግጥምን ጉዳያቸው አድርገው የተሠሩ ጥናቶች

እነዚሁ ብቻ ናቸው ለማለት አልደፍርም። ምክንያቱም እንደ አጥኚ ያልደረስኩባቸው እና በተለያየ ምክንያት ለጊዜው ያላገኘኋቸው ጥናቶች እንዲሁም አርቲክሎች ሊኖሩ ይችላሉ።

ያገኘኋቸው ጥናቶች በተጠኑበት ዘመን ቅደም ተከተል መሠረት፡- ሊሻን ተራራ ‹‹የአስናቀች ወርቁ የፍቅር ዘፈኖች ግጥም ቅርጽ እና ይዘት ትንተና›› (1974)፣ አንተነህ መርዕድ ‹‹ከ1975 - 1979 ዓ.ም በገበያ ላይ የዋሉ አማርኛ የዘፈን ግጥሞች ይዘት ቅኝት›› (1980)፣ ሳለው ሳልለው ‹‹የአያሌው መስፍን ዘፈኖች የይዘት ትንተናና የሴተኛ አዳሪዎች አተያይ›› (1982)፣ ጠጅቱ በሬቻ ‹‹ከ1983 - 1986 ዓ.ም

ሦስተኛው ወንዶች ባቀነቀኗቸው የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ሴት እና ተያያዥ ጉዳዮች ለምሳሌ፡- ውበት፣ አካል፣ ሰብዕና የተሳሉበትን ቀለም እንዴትያለነት ለማወቅ ያለኝ ጉጉት ማየል ነው። ይኸውም ወንዶች ሴቶችን የሚያዩበትን (የሚቀርጹበትን) ሁኔታ ለማወቅ በማሰብ ነው።

በገበያ ላይ የዋሉ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች መዘርዝር፣ ስብሰባና አሃዛዊ ትንተና›› (1987)፣ አብነት ስሜ ‹‹የይልማ ገብረ አብ የሌሪክስ አጻጻፍ›› (1988)፣ ሰላማዊት ይልማ ‹‹ከ1987 - 1990 ዓ.ም በካሴት ታትመው በገበያ ላይ የዋሉ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ቅርጽ እና ይዘት ትንተና›› (1991)፣ ሚካያ በኃይሉ ‹‹የውስጣዊ ሰብዕና አቀራረጽ በሶስና ታደሰ የዘፈን ግጥሞች ወስጥ›› (1996)፣ ወርቂቱ ቱፋ ‹‹የዘማሪ ይልማ ኃይሉ የመዝሙር ግጥሞች ይዘትና ቅርጽ ትንተና›› (1997)፣ መላኩ ጌታቸው ‹‹የእጅጋየሁ ሽባባው የዘፈን ግጥሞች ይዘት ትንተና›› (1998)፣ አለምሰገድ አበበ ‹‹ቅርጽና ይዘት

ትንተና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነጋድራስ እሸቴ ባሳተሟቸው የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ›› (1998) የሚሉት ናቸው።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል የጥናቱ ዓላማ የሚያሳዩ ሁለት ቁልፍ እና ሌሎች ንዑሳን ጉዳዮች በእንስታዊ የሥነ-ጽሑፍ ሂስ ተተንትነዋል፡፡ እንሱም:- ጥናቱ ባካለለው ዘመን እና የዘፈን አልበሞች በወንዶች በተደረሱ ግጥሞች ውስጥ የሴት ውስጣዊ ገጽታ ባካለለው ዘምን እና የዘፈን አልበሞች በወንዶች በተደረሱ ግጥሞች ውስጥ የሴት ውስጣዊ ገጽታ እና የሴት ውጫዊ (አካላዊ) መልክ ይሚሉት ናቸው፡፡

### 3.1. ከ2010 እስከ 2012 በታተሙ የዘፈን አልበሞች ውስጥ የሴት ውስጣዊ ገጽታ

በዚህ ክፍል ከ2010 እስከ 2012 ከታተሙ እና በተመረጡ ሥድስት አልበሞች ውስጥ በወንዶች የተደረሱ 12 የዘፈን ግጥሞች ትንተና ቀርቧል፡፡ በትንተናውም የሴትን ውስጣዊ ጉዳዮች የተመለከቱ ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡ በዚህም መሠረት ወንድ ገጣሚዎች "የሴት ውስጣዊ አመለካከትና አኗኗር ይህ ነው" ያሏቸው ጉዳዮች ተተንትነዋል፡፡

ሴት በተናጠል የምታደርገው ክፉም ሆነ መልካም ሥራ የሚዳኘው በማኅበረ ልማዱ የጋርዮሽ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህም ማኅበረ ባህሉ መልካም ብሎ የደነገገውን መስመር ተከትላ ከሄደች ጥሩ፤ ማኅበረ ባህሉ ብልሹ (አይነኬ) ያለውን ብትሞግት፣ ብትጠይቅና ብትቃወም ሴቶችን ሁሉ ወክላ ትወገዛለች፡፡ ይህን ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለችው ሔዋን ታሪክ ያጠናክረዋል፡፡ አዳም የተከለከለውን እጸበለስ እንዲበላ ማድረጓ እና በእሷ አማካኝነትም ሞት ወደ ዓለም መምጣቱ ይገለጻል፡፡ በዚህም በማኅበረሱ ውስጥ ሴቶች እንደ አሳሳች፣ ከሃዲ፣ የማይታመኑ ሆነው ሲቆጠሩ ይታያል፡፡

የእንስታዊያን ንድፈ-ሐሳብ አቀንቃኞች በበኩላቸው ሴቶችን እየገለጸ ያለው ልማድና ባህል ተጽዕኖ ያደረገበት አባታዊው ቋንቋ ነው ብለው ይሞግታሉ፡፡ በዚህም አንዳንድ በጾታ የማይወሰኑ ሁላዊ የሆኑ ባህርያትን ለሴቶች የመስጠት ሁኔታ በግልጽ ይታያል ይላሉ፡፡

ቀጥሎ በቀረበው የእሱባለው ይታየው ግጥም ውስጥ ያለችው ሴትም በፍቅር ግንኙነት ሂደት ላይ ሴት ከሃዲ፣ የአፍቃሪን ቅስም የምትሰብር፣ ፍቅርን ረግጣ የምትሄድ ግዴለሽ ሆና ተስላለች፡፡ እንደ እንስታዊያኑ እሳቤ ግን ክህደት፣ የተሻለ መፈለግ እና ከነበሩበት ዐውድ መውጣት የሴት ሳይን የሰው ባሕርይ ነው፡፡

የገባኝ መሄድ መራቋ፣

ገልጻ ሳትነግርኝ ጥፋቴን፣

አውጥታ ጣለችው እምነቴን፤

ለሰሚው ግራ ነው የሷ፣

ሳምናት የከዳኝ ልቧ። (እሱባለው፣2010)

በግጥሙ ውስጥ ሴት የማትታመን እና ለወንዶች መጥፋትም ሰበብ ሆና ስትቀረጽ በአንጻሩ ወንዱ በስጋም ሆነ በህሊና ንህጹህ ሆኖ ቀርቧል።

ሰው አምኜ መከዳቴ፣

ብታሳየኝ የእውነት ዕዳ፣

ሳምናት ነው የከዳችኝ ሳምናት፣

ስወዳት ነው የሄደች ስወዳት፣

ሳምናት ነው የከዳችኝ ሳምናት። (እሱባለው ይታየው፣2010)

በግጥሙ ውስጥ ያለው አፍቃሪ ሴቷን ከሃዲ አለ እንጂ፤ ከእሱ ተነጥላ ለመሄዷ የእሱም ድርሻ ሊኖርበት እንደሚችል አላመላከተም። ይሁን እንጂ ሰው በባሕርይው የተሻለ ነገርን እንደሚሻ ሁሉ ይቺ ሴት የሚበጃትን ፈልጋ ከሄደች ሴት እንደከሃዲ እና ታማኝ አለመሆን ሊሰጣት አይገባም። ኑሮዋን በማሻሻል ስሜቷን ደስ የሚያሰኛትን እንዳታደርግ እና የአንድ ነገር እስረኛ እንድትሆን ሊፈረድባትም አይገባም።

ሰው አይጠፋም ቤትሽ ከእሁድ እስከ እሁድ

ዳስ ጥለሽበታል ላንድ ቀን ላይወርድ

ያላየሽ አይድንም ቀና አይሆንም ቀኑ

የሚል አዋጅ አለ እስኪመስል ሙሉ

አይነጥፍም አይጎልም ማጀትሽ ቢጠጡ ቢበሉ (አለማየሁ ደመቀ፣2012)

ከላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ ያለችው ሴት ደግሞ በአባዊው ዓለም ሥር ሰዶ እንደሚታየው ሴት ምግብና መጥጥ አሠናጂ፣ ዝግጅት አድማቂ፣ ወንድን በሆዱ ለማሰር የምትተጋ ናት።

ይህ ምናልባት አዳም እጸበለሱን ከሔዋን እጅ መብላቱን ተመርኩዞ ወንድ በሴት እጅ መብላትን እንደሚወድ ሊያሳይ ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻርም አዳም በሔዋን እጅ ስለበላ አባታዊው ዓለም እንስቶችን ለጥቅሙ ብቻ እንደሚገለገልባቸው ያስረዳል፡፡ ምግብና መጠጥን አዘጋጅቶ ማቅረብ የእንስት መገለጫ መሆኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ያለውን በማካፈል "እንብላ፤ እንጠጣ" ማለት የለጋስነት፣ የመልካምነት ውጤት ቢሆንም፤ አፍቃሪው ሴቷን ለሆዱ መቅረቡ ግን ትክክል አይመስልም፡፡

በማኅበረ ባህሉ ዘንድ እስካለንበት ዘመን ድረስ ምግብና መጠጥ እያዘጋጀች የምታበላ ሴት መልካም ትባላለች፤ በበርካቶች ትወደዳለች፤ ዝምድናዋም ይፈለጋል፡፡ እንደተወደደች እንድትዘልቅም የማኅበረ ባህሉ እስረኛ መሆን ይጠበቅባታል፡፡ በተለይ በኢትዮጵያ ገጠራማው አካባቢ ሴትነት የሚለካው ምግብ አጣፍጦ ከመስራት፣ ሌሎችን ከመንከባከብ፣ ከጽዳት ሥራዎችና መሰል ወደ ዐደባባይ እንዳትወጣ ከሚያደርጉ አሳሪ ሁኔታዎች ጋር የተጣባ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ያለች እንስት አጉራ ዘለል ትባላለች፡፡

ከላይ በቀረበው ግጥምም አፍቃሪው ወንድ የምታበላውን እንስት ሽቶ ያንቆለጳጵሳል፡፡ ውዳሴው የመነጨው ሴቷ ካላት ማንነት ሳይሆን ማህበረሰቡ ባስቀመጠው የልማድ መስፈርት ነው፡፡

እንዲህ ያለችው ሴት በእንስታዊያን ዐይን በአባታዊው ዓለም ውስጥ የወንዱን ዓለም የቀና ለማድረግ የተቀመጠች እንጂ የራሷ ዓለም፣ አስተሳብ እና ፍልስፍና የሌላት ናት፡፡ ይህን ደግሞ በጽኑ ይኮንኑታል፡፡

ከእሁድ እስከ እሁድ የሚለው ግጥምም በዚህ ንድፈ ሐሳብ ዕይታ በአባታዊው ዓለም ሴቶች ለወንዶች የተፈጠሩ መሆናቸውን እንጂ ሴትን በእውቀቷ ያልለካ፤ ወደጓዳ የሚስባት ሆናል፡፡ ወንዱ ለሆዱ ተሸንፎ የምግብ ባለሙያዋን ማፍቀሩ ተገቢ አይመስልም፤ በሐሳብ፣ በማሰላሰል፣ በአመላካከት እና ስለዓለም ስላላቸው መረዳት በመግባባት ሊሆን ይገባል፡፡

> እስከ እሁድ ሰው እንዲህ መውደድ፣
>
> እንዴት ተብሎ ያንን ሁሉ አባብሎ፣
>
> ካንድ እሁድ እስከ ሌላ እሁድ፣
>
> ግብዣ ተያይዟል ፍቅር ካንቺ አፀድ፡፡ (አለማየሁ ደመቀ፣2012)

ግጥሙ በእንስታዊያን ዐይን አሁንም ሴቷ ከምታከናውነው ነገር በመነሳት ጾታዋን መግለጽ የፈለገ ይመስላል፡፡ እንስታዊያን ነገረ ጾታን ከድርጊት በመነሳት ጾታ መግለጽን ይነቅፋሉ፡፡

ንገሪኝ እንደምን ከርመሽ ይሆን፣

ከማን ጋር ውለሽ አደርሽ ይሄን ሰሞን፣

ማነው ባለሳምንት ተረኛሽ፣

ተረጋግቶ ሊኖር ያሰበ እንደኔ ሚያጣሽ፡፡ (ጎሳዬ ተስፋዬ፣2012)

በዚህ ግጥም ያለው ወንድ በተረጋጋ ሁኔታ ለመኖር ያሰበ እና ባልተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ ያለ ነው፡፡ የአለመስከኑ ምክንያትም ፍቅረኛውን ማጣቱ ነው፡፡ ይህም በሴቶችና በወንዶች የጋራ አለም ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ ያለውን አቅም ያሳያል፡፡ ይህም በፍቅር ውስጥ የተናጠል አለም እንደሌለ፤ አንዱ በሌላው ሕይወት ላይ ያለውን ዐሻራ የሚገልጽ ነው፡፡ የሴቷ መልካምነት ሲርቀው ሕይወቱ ተናግቷል፡፡

ያለቀልብ አቡክተው ያበሰሉት ያህል ጠረኑ ቢጠራ፣

ትርፉ ቃር አይደል መች ሰውነት ሊሆን የገፉት እንጀራ

ላትኖሪበት ነገር አስር ቤት ለመስራት አስሩን ስታይ

የእግዜሩ እንዳይጠፋሽ መብረሩን አቁመሽ ተረጋጋሽ ወይ፡፡ (ጎሳዬ ተስፋዬ፣2012)

ሴቶች አስተዋይ መባል የሚችሉት ዝምታ፣ መረጋጋት፣ ማብላት፣ መንከባከብ ሲችሉ እንደሆነ በግጥሙ ተደንግጎባቸዋል፡፡ ከላይ የቀረበው ግጥም በሴትነቷ ልትሰራቸው የምትገደዳቸው ብቻ ሳይሆን ስራው ሲከናወን በምን አኳኋን መዘጋጀት እንደሚገባም ይገልጻል፡፡ ማቡካት ብቻ አይደለም ከእሷ ባህሉ የሚጠብቀው፤ ስታቦካ መረጋጋት አለባት፡፡ ይህች እንስት ይህን ባታደርግ ባህሉ ብቻ ሳይሆን በባህሉ ንቃት ውስጥ የተፈጠረው ፈጣሪም እንደሚቀጣት ቀርቦባታል፡፡

ገጣሚው የሳላት ሴት በፈቀዷ መሄዷ የሚያስደንቃት መሆን ሲገባው፤ በአባታዊው ሕግ መሰረት ፈጣሪ የሚቀበላት ሴት እንዳልሆነች አፍቃሪዋ ይነግራታል፡፡ ጽድቅና ኩነኔዋ

የሚወሰነውም ለወንድ በምታደርገው ነገር ተለክቶ እንደሆነ አባታዊው አለም ደንግጎባታል፡፡ የእግዜሩም ፈቃድ ሴትን ለወንድ ምቹ እንድትሆን የሚያስገድድ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ገና በጊዜ በቀዬው አድባር አብረን አድገን

ክፋት በሌለው በንፁህ ፍቅር ተፈላልገን

ተዋደን ኖረን ባልነበር አይነት በሚያስቀና

ልቧን ከልቤ ድንገት ለያየን ቀን መጣና (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2010)

እዚህም ግጥም ውስጥ ሴቷ ያለችው እንስት ታማኝ አይደለችም፡፡ የሴቶችን ማንነትና ምንነት የሚገልጹ የወንዴ ብዕሮች የሴትን ምስል አሉታዊ አድርጎ ማቅረብ አለማቅረቡን ስለ ሴቶች ወንዶች ደጋግመው የሚያነሷቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ደጋግመው ከሚሰሙት ጋር አንድ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን ከላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ ያለችው እንስት የወንድ ብዕር ያጨለማት ሳትሆን  በውጫዊ ወሬ እንደለያት ይናገራል፡፡

ቀና አታርጉኝ እኔን ከሄደች ጥላው መማፀኔን

ጨለማ አልብሳው ስትሔድ የፈካው ቀኔን (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2010)

በዚህ ግጥም እድል የምታጨለም ገጸ ሴት ቀርባለች፡፡ ይሄ ሴት የምትሳለበት ልማድ ሄዋን እንደ አሳሳች ከማየት የተቀጠለ ታሪክ ሳይሆን የሴቷን ልዕለ ሀይል የሚያሳይ ነው፡፡ በእንስታዊያን ዐይን ግን ለወንዶች የነበረችው እንስት ለራሷ ለመሆን ከአባታዊው ግዞት እስራት እራሷን ነጻ ያወጣች እንስት ትታያለች፡፡

እኔስ አቅም የለኝም እባክሽ ብዬ ልመላሳት

ቢፈጀው እግሬን የፍቅር እሳት

አይሞከርም መቼም እሷን ለመርሳት (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2010)

በዚህ ግጥም ውስጥ የእሷ ሕይወት አጨላሚነት እና ከሃዲነት በማሳየት እንዲህ ያለችውን ወንድ ለመውደድ የሚችል ባለ መለኮታዊ ልብ አድርጎ ራሱን አስቀምጧል፡፡ በዚህ ትረካው ስለወንዶች በጎ ሰብዕና በማመልከት የሴቲቱን የክህደት ምስል ያጎላል፡፡

የእንስታዊ ሴቶች ማንነት በወንዶች ዓይን እና ቋንቋ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ሴት እራሷ የሆነችውን አባታው ልማድ  ቀምቷታል፡፡ እንስታዊያን ሴቶች በቋንቋ እና በባህል ውስጥ የረሳቸውን አለም እንዲፈጥሩ ይሞግታል፡፡

ሆድዬ ተይ አውጊኝ ምሽቱ ሳይነጋ

ልቤ እንዲረጋጋ

አንቺዬ ከነጋማ ወዲያ ብራ ነው

ተይ አውጊኝ ገና ነው (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2010)

በዚህ ግጥም ውስጥ እንስቷ በወንዱ አስቸጋሪ ጊዜ ረዳቱ ሆና እንድትቆይ ይፈልጋሉ። ጨላማ በፈሊጣዊ ፍችው ክፉ ቀን ማለት ነው። የእሷን አስፈላጊነት እሱን የሚያስጨንቀው ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ ነው። "አንቺዬ ከነጋማ ወዲያ" ይላታል። "ከማንም ስኬታማ ወንድ ጀርባ ሴት አለች።" የሚለው የአፍሪካዊያን ተረት አይነት ሴቶችን የወንዱን አለም ለማቅናት አጋዥነታቸውን የሚያበረታታ ነው። በግጥሙ ውስጥ ይህ የወነድ ህሳቤ ፍንትው ብሎ ቀርቧል። የእሱ ቀን እስኪመጣ ድረስ በጣም ይፍለጋታል። መድረስ የሚፈልግበት ቦታ እስኪደርስ ድረስ እሷ የምትጠቀመው እቃ ናት። እስከ መጨረሻው ባለው ሕይወቱ ግን እንድትዘልቅ አይፈልግም። ሲነጋ እና ሲሳካለት ያለእሷ መኖር ይችላል። እንስታዊያን አባታዊው አለም እንስቶችን በራሳቸው አልም ለጥቅማቸው እንዲሆኑ አድረገው በባህል፣ በህግ ፣በእምነት አስረው ማንነታቸውን ቀምተው ተጠቅሞውባቸዋል ከሚሉት ሀሳብ ጋር ማመሳከሪያ ይሆናል። በዚህም በወንዶች የስኬት ጀርባ ያሉ እንጂ የራሳቸው ስኬት እና ግብ እነዳየኖራቸው ተደርገው በባህል የተፈጠሩትን እንስቶች በግጥሙ ውስጥ ከስቷል።

ከነጋማ ወዲያ ፀሐይ ከደመቀ

ምንም ሳላወጋሽ ሌሊቱ ካለቀ

ኋላ ብትናፍቂኝ ተጠያቂው ማነው

ዐይንሽ ቀን ከሌሊት አልሰለችህ አለኝ ባየው (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2010)

ገጣሚው ከእንስቷ ጋር ማድረግ የሚፈልገውን ነገር በጭለማ ውስጥ ነው ማድረግ የሚፈልገው። ከሴቷ ጋር የሚኖረውን ግኙኑነት በጨለማ ነው ማድረግ የሚፈልገው። ጨለማ በፍካሪያዊው ፍች የኃጥያት ስራ የሚወክል ሲሆን ንጋት፣ ብርሃን የጽድቅን ስራ ይወክላል። ወንዱ ከሴቷ ጋር ማሳለፉ ከፈጣሪ ጋር የሚለየው አድርጎ ይቆጥረዋል።የእሷ ስራ እና ጥንካሬ በብረሃን እንዲታይ አይፈልግም። እስኪሳካለት፣ ያሰበው ቦታ ደረሶ ስኬታማ እስኪባል ድረስ በስወር ህይወቱ ከእሷ ጋር ነው። በእሷ ስራና ታሪክ ነው የሚኖረው። በብረሃና እና በሚታየበት ጊዜ ግን ብቻወን ነው መቆም የሚፈልገው። ይሄ ሁሌም እንስቶችን ወደ ኋላ

በመግፋት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ወንዳዊውን ስርዓት እና ሃይማኖታዊ አስተምሮ የሚያሳይ ገጸ ባህሪ ነው፡፡

ታምር አርጎ ፈጥሮት ያንቺን ሰውነት
ይኸው እኔ ምኖራለሁ በምድር ገነት
በፍቅር በውብ ሰገነት
አክብሬሽ ሆነሽ ኩራቴ

ቀዳማዊ ነሽ እመቤቴ (ቢኒያም እሸቱ እና ጸጋው ተክሎ፣2011)

በዚህ ግጥም ውስጥ ያለችው ሴት አዲስ ሴት ናት፡፡ አፍቃሪዋ በምድርገነት እሱ የሚኖረው በእሷ ምክንያት እንደሆነ ያናገራል፡፡ እዚህ ላይ ያለችው ሴት ገነትን በማንነቷ የምትፈጥር እንጂ ከገነት ያስባረረች አይደለችም፡፡ እንደሌሎቹ ገጣሚያን ከገነት የወጣባት አሳሳቸው ስለሆነች እንስት ሳይሆን ገነት የምትፈጠር ውስጥ ሴት ተተርካለች፡፡ ይህች ሴት ገጸ ሰብ ከአፍቃሪው ገጸ ሰብ እንድትቀድም ይፈቅድላታል፡፡ ስለዚህ አሁንም ቢሆን ደረጃዋ የሚለካው በወንዱ ነው፡፡ ቀዳሚም ሁለተኛም የምትሆነው በወንዱ አለም ይሁንታ ነው፡፡

እንደ ወይን ሐረግ ፍቅራችን ፀድቆ
የገነት አምሳል ባረግሽ ውቤቴን
ሰረገላው ላይ ከብረሽ ኑሪልኝ
የልቤ ንግስት ቀዳማዊቴ
ቀዳማዊቴ ነሽ ቀዳማዊቴ (ቢኒያም እሸቱ እና ጸጋው ተክሎ፣2011)

በዚህ ግጥም ውስጥ የታሪኩ ባለቤት የሚገልጻት ሴት ከአባታዊው አለም ንቃት ውጪ የሆነችን ሴትን ሳይሆን በሴት ታጥቷል ብሎ የሚያስበውን ገነት፣ የምቾት አለም መልሳ እንድትሰጠው ነው የሚማጸናት፡፡ ከልማዳዊው መመዘኛ ሙሉ ለሙሉ ያፈነገጠ አዲስ መመዘኛ ይዞ የተከሰተ አፍቃሪ አይደለም፡፡ በሴት ታጥቷል ተብሎ በልማድ የተማረውን አለም ሴቷ እንድትመልስለት እየጠየቀ ነው፡፡ አዲስ የእንስትን ምስል የያዘ ግጥም አይደለም፡፡ ፍቅራቸው የጸና እንዲሆን እሷ የማህበረ ባህላዊው ሴት መሆኗ ጥያቄ ውስጥ አልገባም፡፡ ከእሱ በላይ ሆና ቅድሚያ እንድትይዝ የሱ ፈቃድ የተቸራት እሱ ባይፈቅድ ግን የማታገኘው እንደሆነ፣ የራሱን የበላይነት በቋንቋ ውስጥ ደብቆ ያስቀመጠ ወንድ ገጸ ሰብ ነው፡፡ የእሷ የበላይነት እሱ እንዲወዳት እና በበላይነቷ ጸንታ እንደትኖር ከመፍቅደም በላይ አስተዳዳሪ ሆና ለመቀጠሏ " ሰረገላ ላይ ከብረሽ ኑሪልኝ " እያለ እሱ እውቅና ይሰጣታል፡፡ እሱ ካልሰጣት ግን

ራሷ ማግኘት የምትችለው የእሷ አለም የለም፡፡ መስጠት፣መከልከል፣ ማስቀደም ፣ማስከተል በ በዚህ ግጥም ከወንዱ ገጸ ሰብ እጅ አልወጣም፡፡

በሚያውቀው ልብሽ እያስተዋልሽው
ሁለመናዬን ሁለመናዬን ፍቅር አጥምቀሽ
ዳግም ሰራሽው (ቢኒያም እሸቱ እና ጺጋው ተክሎ፣2011)

ይሄ አፍቃሪ ገጸ ሰብ እንስቶች ማህበረባህሉ አእምሮ ውስጥ የጻፉበትን ምስል በሙሉ በማጥፋት ስለ ሴት አዲስ ስዕል እና አዲስ ታሪክ እንደፈጠረችለት ይመሰክራል፡፡ "ዳግም ሰራሽው" እያለ ለአዲስ እይታ እና ለአዲስ አለም እንዳበቃችው ይናገራል፡፡ ይህ እንስቷ ረብ ያላት እንደሆነች ያረጋግጥላታል፡፡ ረብ ያላት የተደረገችው ግን የወንዱ ገጸ ሰብ ህይወት ምቹ ከማድረግ አንጻር ነው፡፡ ይህም የሴትን ምስል አዳምነው ከሳሉበት ማህበረሰብ ነጻ እንድትወጣ አሁንም የወንዶች ምስክርነት አስፈላጊ እንደሆነ ይታይበታል፡፡፡ በዚህም በእንስታዊያን ስነ ጽሁፍ ሂስ የእንስትን ምስል በአዲስ መልክ ለመሳል አሁንም ድረስ ጥያቄ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርገዋል፡፡

አዎ ልክ እንደናቴ

ግርማ ሞገሴ ነሽ ግርማ ሞገሴ
የምሳሳልሽ አዎ ልክ እንደናቴ
እንደ ፋኖስ ጨለማው በብርሃን
ፍቅር ሞልታ (ቢኒያም እሸቱ እና ጺጋው ተክሎ፣2011)

በዚህኛው ግጥም ውስጥ "እንደፋኖስጨለማውበብር፣ ፍቅርሞልታ" ይህ ገጸ ወንድ በእሷ ምክንያት በተለምዷዊ ከተያዙበት ለእንስት ያለውን እይታ ስላስቀጠለችለት አፍቅሯታል፡፡ የራሷን ምስል ይዛ መጥታ ቢሆን አይቀበላትም፡፡ "ልክ እንደ እናቴ"እያለ ማህበረባህሉ የፈረጃትን ሴት እሱም በዛው መስፈርት እንደትቀጥል የማህበረ ባህሉን ሴትነት ይጭንባታል፡፡ ይህች ሴት ወደ ራሷ ምስል ወደ ማንነቷ አትወስደውም፡፡ እንስቶችን በአንድ አይነት አመለካከት ይመለከታቸው እንደነበረ "የምሳሳልሽአዎልክእንደናቴ" በማለት ስለ እሷ ያለውን ተለምዷዊ አመለካከት ለመተው እንደ ፋኖስ ጨለማውን በብረሃን ቀይራ በማለት ስለእሷ አዲስ እይታ እንዳይኖረው በእናቱ ማንነት ያስራታል፡፡

አረ እንዴት ነሽ አረ እንዴት ነሽ

የምን ሳቅ ጨዋታ ደግ ተሸኝቶ

ቀዬውም መንደሩም ተክዞ ሰንብቶ

የተፈጥሮ ነገር የውበትም ነገር

አንቺን ናፍቆ መዋል አንቺን ናፍቆ ማደር

አረ እንዴት ነሽ አረ እንዴት ነሽ (አበበ ብርሃኔና ናትናኤል ግርማቸው፣2012)

እዚህ ላይ ያለው ገጸ ሰብ ወዳጁን መናፈቁን ናገራል፡፡ መሄዷ ያሰሰበው ሴት አታላይ ተደርጋ የተሳለች እንስት አይደለችም፡፡ ፈቃዷን ለማድረግ የሄደች እንጂ፡፡ በመሄዷ እሷ ያጣቸው ነገር ሳይሆን እሷ በመሄዷ ያጣው ነገር ተዘግቧል፡፡ "የተፈጥሮ ነገር  የውበት ነገር" በ በማለት እንስቷ በባህል ተጽዕኖ ስር የሌለች እና ተፈጥሮአዊ ፍቃዷን በመምርጥ አካባቢው፣ ልማዱን ትታ የሄደች ገጸ ሴት ትገኛለች፡፡ አፍቃሪ ገጸ ሰብ ለአካባው እና ለሰፈሩ ተናፋቂ እንደሆነች በመግለጥ ወደ ሰፈሩ እነድትመለስ፣ ወደ ልመዱ እንትመጣ ሳይሆን ባለችበት ሆኗ ስለ ደንነቷ ለመስማት ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱ የእሷ መሄድ ለእሱ እና ለአካባቢው ትሰጥ የነበረው አገልግሎት ተቋርጧል፡፡ የእሷ በእሱ እና በህብረተሰቡ መሃል መገኘት የእሷ ማንነት መገኘት ሳይሆን ጉድለትን በመሙላት ልማዳዊውን አለም ሙሉ  የማድረግ ናፍቆት ነው፡፡

ደስ አለኝ እመጣለሁ ስትይ ሰምተዋል መሰለኝ

ደስ አለኝ ዘማመሩ ወፎቹ ዜማቸው ደስ አለኝ

እመጣለሁ ስትይ ሰምተዋል መሰለኝ ደስ አለኝ

ዘማመሩ ወፎቹ ዜማቸው ደስ አለኝ (አበባው ብርሃኔ እና ናትናኤል ጌታቸው፣2012)

ከላይ በራሷ ፈቃድ ከአካባቢው የሄደች እንስት በዚህኛው አዝማች ወደልማዱ ለመመለስ እመጣለሁ ትላለች፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ ሁሉንም ድርጊት በራሷ የምትፈጽም እንስት ሳትሆን ያጎደልችው የተለምዶ አለም መልሳ ለመሙላት በልማድ ስትሸነፍ አፍቃሪው ገጸ ሰብ ሲደሰት ይታያል፡፡ እራሷ ሄዳ እራሷ የመጣች፡፡ የወንድ አፍቃሪው ድርሻ ስትሄድ የሚሸኝ ስትመጣ የሚቀበል መስሎ የቀረበ ሚመስልም በጥልቀት ግን ከጎደለችበት የወንድ አለም ተመልሳ ስትመጣ እና ወደልማዱ ስትመለስ ትታያለች፡፡ በዚህም ለእንስቷ ሙሉ ለሙሉ ፍቃዷን

የተወላት እና ጣልቃ የማይገባ ሆኖ ከመቅረብ ይልቅ የራሷን ፈቃድ ልታደርግ ብትወስንም ልማዱ መልሶ እንደሚጥላት፣ ተሸናፊ እና ማህበረ ልማዱን መቼም የማታሸንፈው አቅመ ቢስ እንደሆነች ተደርጋ ተቀርጻለች፡፡ እዚህ ግጥም ውስጥ የሚታየውም ውበት አካላዊ ሳይሆን ማንነት ሆኖ ቀርቧል፡፡ በእንስታዊያኑ እይታ የሴቷ አለም የተመለሰበት እና ሴቷ ነኝ የምትለውን የኖረችበት ሳይሆን ወንዴውእንስቷ ከራሷ አለም ለመመለስ የልማድን የበላይነት ጫነ እንዲያሳይ የተደረገበት እንደሆነ ያዩበታል፡፡

ኖረሻል ኖረሻል እንዴ
ላንቺማ ኖረሻል እንዴ
ተጠራሁ ባንቺ ማንነት
ስምሽን አቤት አልኩበት (ቢኒ ባና እና ኤሊያስ ግዛቸው፣2011)

በዚህ ግጥም ውስጥ የተሳለችው ገጸ ሴት አፍቃሪው ለራሷ ያልኖረችን ሴት እንደወደደ ይናገራል፡፡ ለባህሉ እና ለወጉ የኖረች ገጸ ሴት በማህበረሰቡ መልካም ሴት ትባላለች፡፡ በእንስታዊያን የስነ ጽሁፍ ሒስ እንዲህ ያለችው ሴት ከማንነቷ ተነጥላ ያለች ማንነቷን ማህበረባህል የነጠቃት፣ ያልኖረች እንሰት የሚወድስ ግጥም ነው፡፡ እሷን ለማወደስ የአፍቃሪው ትልቅ ምክንያት ለራሷ አለመኖሯ ነው፡፡ ይህ አሳሳል ሴትን ልጅ ለወንድ ልጅ መፈጠሯን የሚያስተጋባ ነው፡፡ አንዲትን እንስት መልካም እና ጥሩ የሚያስብላት ለወንድ በምታደርገው እንክብካቤ ነው፡፡ ይህን ባታደርግ ፍላጎቷን እና ማንነቷን ማህበረሰቡ ከዘረጋው ትክክል እና የስህተት መርህ ውጪ ብትሆን ስነምግባር የለሽ፣ በወንዱ አለም የምትወቀስ ተደርጋ ትሳል ነበር፡፡ ‹‹ተጠራው በአንቺ ማንነት ያለታል›› ይህቺ እንስት በመወድሱ ለእሱ እንጂ ለእሷ እንዳልኖረች ይነግራታል፡፡ የባህል እስረኛ አድርጎ ለማስቀረት የሚያነሳሳ ነው፡፡ እሷ ለእሱ ከኖረች ብኋላ ማንነቱ እሷ እንደሆነች ይነግራታል፡፡ በእርግጥ ግጥሙ እርስ በእርሱም የሚጣረስ ነው፡፡ ምክንያቱ ለእራሷ ማንነት የሌላት፣ለራሷ የማትኖር አድረጎ የተረካትን መልሶ በእሷ ማንነት እንደትጣራ ይገልጻል፡፡ እሷ ልኬቷ የማህበረሰቡ ማንነት ነው፡፡ ማህበረሰቡ የሴትን ማንነት የፈጠረው ለወንዶች አለም አንደትመች አድርጎ ከሆነ ገጣሚው እሷ ውስጥ ያለው ኑሮ ለእሱ የሚመች ነው፡፡ በዚህም ህይወቷን እንደቀማት ያረጋገጠበት ነው፡፡

ባወድስ ባዜ ምላንቺ
አይበዛም ያንሳል እንጂ
ቀን ቆጥሮ ዘመን ቢለካ
ያንቺን ልብ የለም ሚተካ (ቢኒባና እና ኤሊያስ ግዛቸው፣2011)

ይህች እንስት የለችም። በማህበረባህሉ መልካም ለመባልና ጥሩ ለመባል ሕያውነቷን አጥታለች። በዘመናት በተገነባው ባህልና ወግ እስረኛ የሆነችን ሴት በማወደስ እንስታዊያኑ ቋንቋዎቹን እውነተኛውን የሴት ማንነት እንደማይገልጽ የሚታዘቡበት ነው። አባታዊ የነበረው ዓለም የእንስቶችን ማንነት የመግለፅ ብቃት እንዳይኖረው አድርገው ነው ያካማቹት። ይህ የቋንቋ ክምችት እንስቶችን ለወንዶች ድሰታ እና ግዞት በሚመች መልኩ ነው ያዋቀሩት የሚል ተቃውሞ የሚያስነሳ ነው። አባዊው አለም እንስታዊነትን የሚገልጸው ራሱ በሚፈልገው መንገድ ነው። በዚህ ግጥም የወንዱ የእንስት ሰብዕና መለኪያ ተገልጽዋል።

## 3.2. ከ2010 እስከ 2012 በታተሙ የዘፈን አልበሞች ውስጥ የሴት ውጫዊ (አካላዊ) ውበት

አካል ማለት ራስን ኮፒ የማድረግ ሂደት አይደለም። ሰው ይወለዳል። ራሱን ደገመ የሚባል ቢሆን ኖሮ ማህበረሰብ በየጊዜው አይቀየርም ነበር። የማህበረሰብ አመለካከት እና አስተሳሰብ በየጊዜው ይቀየራል። የእንስትን አካል በተመለከተ በየዘመኑ ምን ዓይነት ተክለ ሰውነት ትኩረት እንደሚሰጠው በየጊዜው ትኩረት የሚሰጠው ተክለ ሰውነት ይቀያራል። በየዘመናቱ በዘፈን ግጥም ውስጥ እንኳን የሴቶችን አካል መሰረት ተደርገው በወንዶች የሚገጠሙ ግጥሞች የዘመኑን ልማድ እስረኛ እንደሆኑ መነሳት ይችላል። ዳሌ፣ ባት፣ ወገብ፣ ተረከዝ፣ ጡት፣ ዓይን፣ ርዝመት፣ ውፍረት፣ ሸንቃጣነት ወዘተ. በየዘመኑ እየተፈራረቁ የሴት ልጅ የአካል የውበት መለኪያ ሆነው አገልግለዋል። ይሄ ገለጻ የሴት ልጅ ተፈጥሮአዊ አካል ሳይሆን ልማዳዊ አካል የሚያሳይ ነው። በየዘመኑ የሚነሱ እና ትኩረት የሚያገኙ የሴት ልጅ የአካል ክፍሎች አሉ።

በዚህኛው ንዑስ ክፍል የቀረቡ መረጃዎች ትንተና የሴቶች ውጫዊ ውበት ተብለው በግጥሞቹ ውስጥ የተነሱ ዕይታዎች እና የሴት ልጅ ውበት የተቀነበበበትን ማዕቀፍ የሚያሳይ ነው።

በዚሁ መሠረት በሴቶች ላይ ውበት የሚባለው ምንድን ነው?፣ በተለይ የሴቶች ውጫዊ ገጽታ (መልክ፣ የአካል ክፍሎች) እንዴት እንደቀረቡ የተዳሰሰበት ነው። በእነዚህ ግጥሞች ውስጥ የሴቶች መልክ በልዩ ስሎች ስዕላዊውን (Graphic) ገጽታቸውን እንጂ ቃላዊ (Verbal) እና ግንዛቢያዊ (Perceptual) መልኮችን በዚህ ርዕስ ጠቅልዬ አልመለከትም። ምክንያቱም በሰብዕና(ውስጣዊ) እነዚህን ገጽታዎች ስለምመለከታቸው ነው።

ይህ ገጸ ሰብ ስለ ተፈቃሪው ውበት ለመግለጽ በቋንቋ መግለጽ መገደቡን ለማሳየት እንደተቸገረ ይናገራል። ይህ ነባሩ የተለመደው ቋንቋ ተፈቃሪዋን ለመገልጽ ተለምዶዋዊው

የቋንቋ መዋቅር   አቅመ ቢስ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚህም ግጥም ተለምዶንና ስርዓትን ያለፈ አዲስ እየታን ስለ ሴት ውበት ለመከሰት የሚሻን አፍቃሪን የሚከስት ግጥም ነው፡፡

ያንስብኛል ይሳሳብኛል ለእኔ

ሆሄ ፊደላት ሰዋሰው ቅኔ

ውበት ቁንጅናሽ በምን ይለካ (እሱባለው ይታየው፣2010)

በሙዚቃው ግጥም ውስጥ ቃላትን በመኮነን ውበት የሚገልጽበት እጥረት እንዳለ ያሳያል፡፡ በዐይን የሚታየውን ውበት በቋንቋ ወክሎ የመሳየት አቅም ስነ ጽሁፋዊ ብቃት ላይ ጥያቄ ይፈጥራል፡፡ በዚህም ስነ ጽሑፍ አጋናኝ ምስል ከሳችነቱን ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ውበት በዚህ ግጥም ውስጥ ቀርቧል፡፡ እንስታዊ የስነ ጽሁፍ ሂስ አንዱ አላማው የእንስቶች ውበት ለመግለጽ ይውሉ የነበሩ ቃሎች ከወንዶች ወሲባዊ እርካታ ጋር ተያይዞ መቅረቡን ይተቻሉ፡፡ በዚህም መሰርተ ይህ ግጥም አዲስ እይታን ለመከሰት ተስፋን የሚያሳይ ነው፡፡  በግጥሙ ውስጥ ያለው ገጸ ሰብ ከልማድ ተላቆ አዲስ አገላለጽ ለመከሰት ችሏል፡፡

እፍኝ ማይሟላ

ዕድሜዬ በዝቶ

ዜማው አምሮልኝ

በአንቺ ተቃኝቶ

መንገዴ ቀና ሕይወቴ ሙሉ

አንቺ ካለሽኝ ተድላ ነው ሁሉ (እሱባለው ይታየው፣2010)

ይህ ስንኝ ያልታሰቡ ወይም ትርጓሜያቸው አንድ ዓይነት የሆኑ ክስተቶች ምሉዕነታቸውን ስለሚያጡ አዳዲስ አገላለጾች ከሴቶች አንጻር እንዲኖር ከመፈለግ የመነጨ ነው፡፡ የእሷን ውበት ለመግጽ  ነባሪውን የቋንቋ ቅንጅት አልፎት የሄደ ገጸ ውበትን የተረካል፡፡  "ዜማው አምሮልኝ በአንቺ ተቃኝቶ"  ይህ ግጥም መለኪያ የሌለው ውበት እንደታየው ያሳያል፡፡ ልዕለ ቋንቋ የሚያሻው ውበት ነው ብቻ ለማለት ሳይሆን፣ የተለመደው ቋንቋ የሴትን ልጅ ውበት ለመግለጽ አቅም እንደሌለው የሚገልጽ ግጥም ነው፡፡ እሷን የሚስልበት ቃላት ማጣቱ በራሱ በቋንቋው ውስጥ ያለውን ሴትን ለመበየን ነባሩን አገላለጽ ለማሻሻል መፈለግንና  ለአዲስ  እያታ ፈቃደኛ መሆንን    ይጠቁማል፡፡ የዚህችን ልጅ ውብ ምስል ለመሳል ለሚፈልግ ቋንቋ መጥፋቱ

አድሎዋዊውን የወንዱን አለም አዳዲስ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመርመር አላማው ያደረገው እንስታዊያን ንደፈ ሀሳብን የሚደግ ነው፡፡ መግለጽ  አለመቻል በራሱ የዚሁ አዲስ ልማድን ለማምጣት የመፍቀድ  ውጤት ነው፡፡ የቃላት እጥረት ያገጠመው ልማዳዊው የሴት ልጅ ውበትን መከሰቻ ቃላት መሻሻል የሚያሻቸው እንደሆኑ የሚጠቁም ስንኝ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ግጥም  እርስ በእርሱ የሚቃረንም ጭምር ነው፡፡ ከላይ ቋንቋ እንደሚያጥረው ቢናገርም፡፡ መልሶ ተለምዶ ጎትቶ ይወስደዋል፡፡ ገጣሚው የተገነባበት የቋንቋ ርዕዮት በዚህ ግጥም የታየውን ጭላንጭል አዲስ አገላለጽ መልሶ ያጨልመዋል፡፡ ግጥሙ የገጣሚው እይታ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡ ውበትን የሚወክልበትን "ውብ"፣ "ነፍስ"፣ "ዐይን"፣ የሚሉ ተለምዶአዊ ቃለታን ማግኘት ይቻላል፡፡

ማሬ ማሬ ማሬ ማሬ

እንደው ነፍስ ነገር ነሽ ለእኔ

ውቤ ውቤ ውቤ ውቤ

እንደው ነፍስ ነገር ነሽ ለእኔ

ቀንቶኝ ዕድሌ በስም በተራ

በፍቅርሽ ብርሃን  ዐይኔ ሲበራ

ማሞገሻ ቃል ላገኝ ብለፋ (እሱባለው ይታየው፣2010)

ይህ አገላለጽ የገጣሚው ውበት የገለጸበት እይታ ማህበራዊ መስተጋብር ጨምሮ ገጣሚው በራሱ አዲስ አገላለጽ ተከስቷል፡፡ በዚህም  ሴትን ልክ እንደ እቃ  ከመሳል ማህበረሰቡ የሚሰጣትን ቦታ ብቻ ተቀብላ መልካም፣ ቆንጆ፣ ጠንካራ ከሆነች በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ ለሚሰጠው ወንድ የፍቅር አጋር ሆና የመኖር ልማድ ለማስቀጠል ሳይሆን ከልማድ ከልማድ እየወጣ  ማሞገሻ ቃል ለማግኘት እንደሚለፋ ይገልጻል፡፡ በዚህ ገለጻው እንስቷን በቃላት ደልሎ ንብረቱ ለማደርግ ሳይሆን  ልማዳዊ የማድነቂያ ስልቶችን ተጠቅሞ አንዳንዴ ደግሞ ከልማድ ለመውጣት እየናፈቀ አፍቃሪው ገጸ ሰብን ያወድሳታል፡፡ "ዐይኔ ሲበራ" በማለት አዲስ አመለካከት እንደጀመረ እና ከልማድ እንደወጣ ተስተውሏል፡፡

እፍኝ ማይሟላ

ዕድሜዬ በዝቶ

ዜማው አምሮልኝ

በአንቺ ተቃኝቶ

መንገዴ ቀና ሕይወቴ ሙሉ

አንቺ ካለሽኝ ተድላ ነው ሁሉ (እሱባለው ይታየው፣2010)

በዚህ ስንኝ አፍቃሪው ገጸ ሰብ ስል ተፈቃሪዋ ለሱ ተድላ ማሚያ ተደርጋለች፡፡ የእሷ አለመኖር ጉድለት ነው፡፡ ህይወቱ ሙሉ ሊሆን የሚችለው በእሷ የእሱ መኖር ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ እሷን ለተድላወና ለእርካታው በመመኘት ሴቶችን ለወንዶች እርካታ የቁስንት ሚናን የሚደግፍ ሳይሆን በአዲስ እያታ የሴቷን ዋጋ እተመለከተ የመጣ እንደሆን ያትታል፡፡ ሴቶች ለወንዶች እርካታ ብቻ ከመሆናቸውም ባሻገር መንገዳቸውን አቅኚ፣ ረዳት፣ ደጋፊ እንጂ የራሳቸው አለም የሌላቸው አድርጎ የማቅረብን አዝማሚያ የሚቃረን አቀራረብ ነው፡፡ የሴቷ እንስታዊ ደረጃ የሚለካው ለወንዱ ገጸ ሰብ በምትሰጠው ፍሰሃ መሰረት፣ ለወንዱ ምቾት በመስጠቷ ቀርቶ በአዲስ እይታ ዐይኑ በርቶ የሚናገረው እንደሆነ ያትታል ፡፡

ዜማው አምሮልኝ

በአንቺ ተቃኝቶ" (እሱባለው ይታየው፣2010)

ከላይ ያለው ስንኝ ይህ አፍቃሪ ስለ አፈቃራት ሴት ንቃተ-ህሊና እሷን ለደስታው እና ለእርካታው ከመመኘት አልፎ የሷን አቅም ተጠቅሞ እሱ ለመወደስ እንደቻለ ጠቅሷል፡፡ የእሷን አቅም ከኋላው አድርጎ እሷ በተቀኘችው ቅኝት የእሱ ዜማ ጥሩ ሆኖ እሷን እና ችሎታዋን አወድሷል፡፡ ብዙዎች የሚያደምጡት ዜማ የሷ ቅኝት ነው፡፡ ገጸ ሰቡ ለሱ ሙሉ ሆኖ መቅረብ እና ተቀባነት ማግኘት የሴቷን እገዛ እውቅና ይሰጣል፡፡ የራሱን ደስታ ለማግኘት ጭራሽ በእሷ ቅኘት እንደተቃኘ እና እሷ ባሳየችው መንገድ ሕይወቱ እንደተቃና ይናገራል፡፡ ሙሉ በሙሉ ለእሷ እውቅና ሰጥቶ ብቻውን መቆም እንደማይችል፤ የሷን ብቃት ተጠቅሞ እሱ እንደደመቀበት ያሳያል፡፡

በአንቺ ሁሉ አለኝ ደስ ደስ

እንግዳ ሆነኩኝ ለአለም እንደ አዲስ

ብቸኝነቴ በአንቺ ኮንኜ

በፍቅር ልቂ ቆምኩኝ ሰው ሆኜ (እሱባለው ይታየው፣2010)

እዚህ ግጥም ውስጥ እሱ ለራሱ አለም መሙያ መሆኗ ቀርቶ እሷን ያካተተውን የጋራ አለም እንደተዋወቀ ይናገራል፡፡ በየዚህ ግጥም ውስጥ ማንም ራሱን የቻለ የሚነገር ሕልውና የሚኖረው ከሌሎች ጋር ባለው መሰተጋብር ነው፡፡ እሱ ከሚያውቀው ላይ ስነ ህይወታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና መንፈሳዊ ተጽዕኖዎች በመስተጋብሩ የሚመጡ ናቸው፡፡ በተወሰነ ደረጃ እያንዳንዱ ሰው የሚኖረው በህይወት ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ሲኖር በሚሰማው ስሜት ነው፡፡ ሲወድቅ፣ ሲጠላ፣ ሲያምረው፣ ሲማርከው፣ ሲያጸይፈው፣ ይህ የህይወት ትርጉም ይሆነዋል፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ “ማሬ” ውብ ሴት እንዳንዴ የሚያጣጥማት፣ አንዳንዴ ቃላት የምታስንቅ፣ አንዳንዴ ደግሞ የአለምን መልክ የምታስቀይር አዲስ መነጽር አድርጎ ስሏታል፡፡ በእሷ አለምን ይነካል፡፡ ከአዲስ አለም ጋር ያስተዋወቀችው ሴት ተደርጋ በእሱ ተገልጻለች፡፡ በግጥሙ ውስጥ ተለምዶአዊውን አለም አላቅቃ አዲስ አለም ስታስነካው አዲሱነም አለም በደስታ እንደተቀበለው ይገልጻል፡፡ የእሷን አዲስ አለም ከማስተዋወቅ ይልቅ የሱን ደስታ በማስቀጠል ለብቸኝነቱ፣ ለደስታው የምታስፈልግ ማንነት አድርጎ በደስታ ተቀብሏታል፡፡

ተገኘሽ ከላይ እንደ ደመና ወይንዬ በቁንጅና

አድናቆት ብቻ አይበቃሽም ቆንጆ ነሽ አልተውሽም (ሰለሞነብ
አንባቸው፣2010)

“ወይንዬ” በሚል ርዕስ በቀረበው ግጥም ውስጥ በተራኪው ገጸ ሰብ የቀረበችው ሴት ውበቷ እጅግ ከፍ ያለ በመሆኑ ፈጣሪ እንደሰራት ይመሰክራል፡፡ እጅግ ያማረው መልክ በፈጣሪ የተሰራ መሆኑን ያረጋግጥላታል፡፡ መልኳ ቢያስጠላ የፈጠራት ከአምላክ በተቃራኒው ያለ እንደሆ የሚጠቁም ነው፡፡ ይህም አፍቃሪው እሱ የሚወደውን ፈጣሪ እንደሚወድ፣ ለእሱ ውበ አድርጎ የሚፈጥረለት ፈጣሪ እንደሆነ በማሳየት ፈጣሪ ከወንዶች ጋር የሚሰራ አድሎዋዊ እንደሆነም ይመሰክራል፡፡ ይህም ፈጣሪ የወንዶች ወዳጅ እና አብሮ ሰራተኛ እንደሆነ ለማሳት የሚሞክር ግጥም ነው፡፡

ኧኸ ውብ አርጎ ቢሰራሽ ኧኸ ፈጣሪ ባምሳሉ ኧኸ

ትወዛወዘልሽ ያየሽ ሳር ቅጠሉ ኧኸኸ (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

ቆንጆ በመሆኗ ለእሱ እንደምትገባው እርግጠኛ በመሆን ይናገራል፡፡ ውብ ብሎ የጠራትን ሴት ፍላጎትና ፈቃድ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ‹‹ቆንጆ ነሽ አንቺ አልተውሽም›› በማለት ይዝታል፡፡ በዚህ ስንኝ ውስጥ የወንድ የበላይነት ይስተዋላል፡፡ እሱ የማድረግ ካልፈልገ የመተውም መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ይህ አገላለጽ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡ ‹‹ተዋት፣

ጥሏት ሄደ፣ ፈታት፣ ተለያት›› እንዲህ ያለው አገላለጽ ወንዶች በጾታ ግንኙነት በመቀጠልና በማቆም ያላቸውን የበላይነት የሚያሳይ ነው፡፡ ስለ ሴት ልጅ የሚነገሩ አባባሎች ሴትን የሚያሳንሱበት መንገድ በማስቀረት ለሴት አዲስ ኃይልን የተሞላ የለውጥ ጊዜ ማምጣት ለሚፈልጉ እንስታዊያን ‹‹ቆንጆ ነሽ አልተውሽም›› የሚለው ሐረግ ሴት በአእምሮ ሆነ በአካል የሚያንሱ፣ ተሸናፊዎች ወዘተ. ልማድን ማስቀጠያ እንደሆነ የሚያስተውሉበት እና ቆንጆ በመሆኗ ለተባዕት ንብረት የመሆን ግዴታ እንዳለባት ተደርጋ መሳሏን የሚተቹበት ነው፡፡

> እሽ አይንሽን ለጥቅሻ እሽ ከንፈርሽን ለቅምሻ እሽ
>
> አየሁት በስስት መንገዴን እስክስት እሽሽ
>
> እሽ ውብ አርጎ ቢሰራሽ እሽ ፈጣሪ ባምሳሉ እሽ (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

ውበቷ ወንድን የምታማልልበት አቅሟ አድረጎ ገልጾታል፡፡ አንዲት እንስት ሰውነቷ እራሷን የምትገልጽበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ነገርን ዐይኗ፣ከንፈር፣ ዳሌዋ፣ ጾታዋ፣ መቀመጫዋ ወዘተ. ሴትነትን ለመግለጽ በቂ አይደለም፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ አካላዊ ማነነቷ ልማድ ለፈጠራት ሴት በመግጠሟ ወንዱ እሷን የራሱ ለማድረግ ትልቅ መስፈርት አሟልታለች፡፡

"መንገዴን እስክስት" ይህ ስለ ሴት ውበት ያለውን ልማድ (በተለምዶ አገላለጽ ሴትናቷን ) የምትጠቀም ፣ወንዶችን አሳሳች ተደርጋ የምታየውን ልማዳዊ ሴት እንደወደደ፣ ውበቷን የምትጠቀም ሴትን ያሳያል፡፡ ሴት ወይም ወንድ ብለን በጾታ የምንመድበው መጀመሪያ ውስጣችን በተጻፈው ልማድ መሆኑ አግባብ የሚናገሩት እንስታዊያን ሴቶች እንደ አሳሳች፣ የወንድ መንገድ የሚያስቱ ተደርጎ የመቆጠራችውን ልማድ የሚያረጋግጥላቸው ነው፡፡

> ሰው አለኝ አምላኬ ከሰውም የክት
>
> ተቀምጠሽ ብርሃን ቆመሽ መስታወት
>
> ስከተልሽ አንቺን ከልብሽ ስጠጋ
>
> ታፈርኩኝ እንደባለፀጋ (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

ሙሉ ለሙሉ ማንነቷን ያለ ቅራኔ እንደተቀበለ የሚያሳይ ነው፡፡ ‹‹ታፈርኩኝ እንደባለጸጋ›› ውበቷ ለእሱ ጥቅም አምጪ፣ አትራፊ እንደባለጸጋ ያስቆጠረው ሆኖለታል፡፡ ‹‹ለእኔ›› የሚል ድምጸት አለው፡፡ ይህ ወንዶች ሴቶችን እንደ ደስታ ምንጫቸው እና እንደ መርኪያቸው

የሚያዩበትን እይታ የሚያጎላ ሳይሆን ሴቶችን የሆኑትን ሆነው  የሚቀበሉበትን አዲስ አስተሳሰብ የሚያመለክት ነው፡፡

እንደ ምኩራብ ደውል ነው ለነብስያዬ

ቃልሽ ዘለሰኛ ድምፅሽ መዲናዬ

እህ ስልሽ ኑሪ ነግሰሽ በላዬ ላይ

ፊሰሽ እንደ ክረምት ሞቀሽ እንደ ፀሐይ (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

አንዴ ከጸሎት ቤት ደውል፣ አንዳንዴ እንደ መዲና፣ ሌላ ጊዜ ንግስና፣ እንደ ጸሐይ እያነጻጸረ ያቀረባት ውብ ሴት ከፍ ያለ ሰብዐዕናን ተላብሳ ተስላለች፡፡ እንስቶችን  በዚህ ስነ ጽሁፍ የውብ ሴትን መልክ ለመግለጽ ቃላት ሲያጥር ሳይሆን የነበረ ቃል በሰበበ ንጽጽር የቃላት እጥረት ክፍተትን ሞልቶ የሴት ልጅ መልክ ሲጎላ ይታያል፡፡ ሴታዊነት ማህበረባህሉ በሚሰጠው ልምድ መሰረት  ብቻ ሳይሆን ከዛም ከፍ ተደርጎ  ቀርቧል፡፡

‹‹እዩዋት›› የሚለው ግጥም ላይ አፍቃሪው ያየውን ውበት ሌሎች እንዲያዩት የሚያነሳሳ ነው፡፡ ሴቶችን የምያበትን መንገድ ለማሻሻልና ከልማድ ወጥተው እንዲመለከቷት የልማድ እስረኛ ከመሆ እንዲወጡ  ይጠራቸዋል፡፡ የወንዶችን የበላይነት መቀናጀት ፍላጎት በመተው የፈለገ ገጸ ወንድ ድምጽ ይሰማል፡፡ ‹‹ይሄ የምታዩት ውበት››  የሚል ድምጽ የያዘ ነው፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ ገጸባህሪው የፍቅሩን ውበት ከማሳየት ይልቅ ይህ ውበት እንዲታይ የሚሻ እና ትርጓሜን የሚቀይር ማስተዋልን የሚጠይቅ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ "እዩዋታ" አስተውሏት ለሚለው አቻ ትርሜ ይሆናል፡፡ አዲስ ትርጓሜን ለማመልክት የሚሆን የእይታ ጥሪ ነው፡፡ "የእውነት እዩዋታ" ክልማድ እየወጡ የእውነት የሆነችውን እንዲመለከቷት እንዲተረኳት ይጣራል፡፡ ከልማድ የሚያስወጣ ጥሪ ያቀርባል፡፡

ይሰማኛል ደስታ ከሌሎች አብልጣ

ኮራ እያለች ወደኔ ስትመጣ

አታምርም ወይ ታዲያ የእውነት እዩዋታ

ገና ከሩቅ በአይኖቿ ምትረታ

እዩዋት የልቤ ብዬ ያልኳችሁ እዩዋት የማጫውታችሁ

እዩዋት እኔን ብላ ተገኝታለች ተመልከቷት ያው መጥታለች (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

የእሱ እያታ ስለተሸሻለ እሷ ወደሱ በደስታ እና በፈቃዷ የመጣች እንስት "ያው መጥታለች" ይላታል። "ምትረታ" አሸናፊ ፣ አቅም ያላት፣ እይታ አንዷት ሴት ለወንዱ የልቡን ምኞት ለመሙላት ተለምዶ ባስቀመጠው የውበት መለኪያ ከሌሎች የምትበልጥ ብቻ ሳትሆን እይታዋ አዲስ አስተሳሰብ የተላበሰ "አይኖቿ" አካላዋን ብቻ ሳይሆን አመለካካቷንም የሚከስት አሸናፊ እንስት ተደርጋለች። እሷ ለእሱ ብላ ነው የተገኘችው። ፍቃዷ አለመሆኑን የሚያሳየው ‹‹ለእኔ ብላ›› የሚለው ነው። ይሄ አገላለጽ የሙብት ጥሰት ሳይሆን ለሰው በሚደረግ ነገር ደስታን ለማግኘት መልካም ምግባር የተላበሰችን እንስት ነው የሚከስተው። እሱ የሚፈልጋት ቦታ የተገኘቸው ውብ ሴት በአስገዳጅ እጅ የተገኘች ሳትሆን እሱን ማስደሰት የሚችል ልማዳዊ ሴትነት እንዳላት እርግጠኛ በመሆኗ ነው። ይህች ሴት ከማንነቷ ይልቅ ማህበረሰቡ በሰጣት ማንነት የምትኖር ናት።

በሌላ በኩል ግን ይህን መልክ የተላበሰች ሴት ወጣት፣ ቆንጆ ወንዶችን የማማለል ህልም ያላት ናት። የወንዶችን ደካማ ባህሪ ጠንቅቃ የምታውቅ፣ ይህን እውቀትም በቀላሉ ለማጥመጃነት የምትገለገል ናት።

> ስፍራ ጠብቆ ያንቺ ውበት ጎልቶ ቢታይ ፈክቶ እንደ ፀሐይ
>
> ውብ ያደረገሽ ባይንሽ ዙሪያ ቅንድብ ስሎ ኩል አስመስሎ
>
> እንዴት ታምሪያለሽ ውቤ መሳይ ውበትሽ ጎልቶ ለአለም ይታይ
> (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2010)

ትረካው የቀረበው ማህበረሰቡ ለፈጠራት ሴት እንጂ ሴቷ ውበቴ ጥርስ እና ዐይንና ቅንድቤ ነው ስላለች አይደለም። ይህ የሴትን አካል አድናቂ እሱ የራሱ የሆነ የቆንጆ መመዘኛ ያለው ነው። በዚህም መመዘኛ መሰርት የተኳለ የመሰለ ዐይን የውበት መለኪያ ሆኖ ቀርቧል። በግጥሙ ተፈጥሮ የሚመስል አኳኳል ሳይሆነ ሰው ሰራሽ የመሰለ ተፈጥሮ ተደንቋል። እንስቷ ኩል መስሎ በተሳለው ቅንድቧ ውበቷን በመሳል ተፈጥሮን በሰው ሰራሽ ማሻሻል ይበልጥ የሚበለጽግ አድርጎ ከተፈጥሮ ፈጣሪ ይልቅ ገጸ ሰብ ከመለኮት ከፍ አድርጎ ተስሏል።

> ከከንፈርሽ ላይ ፅጌረዳ ሳይ
>
> ከራሴ ጋራ እስከምለያይ
>
> ብቀር ፈዝዤ ጠፍቶኝ ማረገው
>
> ዐይኔን ካፍሽ ላይ ጣል ባረገው
>
> ሳማት ሳማት አለኝና ቀልቤን ገዛው እንደገና

ሳሙኝ ሳሙኝ የሚል ከንፈር ድንገት አጉል አርጎኝ ነበር (ቴዎድሮስ
ካሳሁን፣2010)

ከላይ የቀረበው ግጥም ውስጥ ያለው ገጸ ሰብ ከንፈሯን ከጽጌሬዳ ጋር በማነጻጸ በከንፈሯ አካል ክፍል እንደሳበችው ይናገራል፡፡ እዚህ ላይ ያለችው ማራኪ እንስት ሳቢ ያደረጋት በራሷ ሰርታ ባመጣቸው አካል አይደልም፡፡ ከንፈሯ ለማማሩ የእንስቷ ተግባር ወይም እጅ የለበትም፡፡ በጾታ የተቀበለችው የአካል ክፍል ቢሆን ሰውነቷ ምርጫዋ ሆነ ማለት ነው፡፡ ለሌሎች እንስቶችም ሰውነት ምርጫ እየሆነ ይመጣል፡፡ ግን እዚህ ግጥም ውስጥ ያለችው እንስት ከንፈሯን እንደ አካሏ እንጂ እንደ ውበቷ ባትቀበል የገጸ ባህሪው አድናቆት ዋጋ ቢስ ነው፡፡

> ...The body of woman is one of the essential elements of her situation in the world.Butthat body is not enough to define her as woman; there is no true living reality except as manifested by the conscious individual through activities and in the bosom of a society" (Butler,2021;41).

ኧኸ አይንሽን ለጥቅሻ ኧኸ ከንፈርሽን ለቅምሻ ኧኸ

አየሁት በስስት መንገዱን እስክስት ኧኸኸ

ኧኸ ውብ አርጎ ቢሰራሽ ኧኸ ፈጣሪ ባምሳሉ ኧኸ

ተወዛወዘልሽ ያየሽ ሳር ቅጠሉ ኧኸኸ (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

ይህ የእንስት አካል አፍቃሪው ገጸ ሰብ "ዐይን ለጥቅሻ" በማለት አይኗን ለመመልከት ሳይሆን ለማማለል ተግባር እንድታውለውና ከንፈሯን ደግሞ ለመቅመስና የፍላጎቱ ማርኪ እንዲሆን አድርጎ ተርጉሞታል፡፡ ዐይኗን ለጥቅሻ ከንፈሯን ለመሳም በዚህ መንግድ የተሰጠ ነው፡፡ እንስቷ በአካሏማግኘት የሚፈልገውን እርካታ ያሳያል፡፡ የምታደርገው፣ ልትይዘው የሚገባ ቅርፅ፣ የምትለብሰው፣ አኳኋኗን እንዲህ መሆን አለበት እንድንል ያስተማረን ልማድ ነው፡፡ ሴትን ሰውነቷ እንዲገልጻት ተደርጋለች፡፡ ይህ ልማድ እሷን አይገልጻትም፤ ማህበረሰቡ በርዕዮቱ የፈጠራትን ሴት ነው የሚገልጻት፡፡

ይሰማኛል ደስታ ከሌሎች አብልጣ

ኮራ እያለች ወደኔ ስትመጣ

አታምርም ወይ ታዲያ የእውነት እዩዋታ

ገና ከሩቅ በአይኖቿ ምትረታ (ሰለሞን አንባቸው፣2010)

ይህ ገጸባህሪ የተረታላት እንስት እሱ የተረታላት ሳይሆን እሷ እንደረታችው ነው የሚገልጸው። በዚህም እሷ ረቺ ለመሆን መፈለጓን ያሳያል። ዐይኗን የፍላጎቷ ማሳያ በማድረግ ድርጊቷ ላይ ፍላጎቷ መታየት ሲጀምሩ ያ የሷን ማንነት ይገልጸዋል። በዚህ ግጥም ውስጥ የተቀረጸችው ገጸ ሴት ፍላጎቷ በአካሏ ገለጸች እንጂ አካሏ እሷን አልገለጻትም። እዚህ ላይ ያለው የሴት ዐይን ሳይሆን ሴት ፍላጎቷን የገለጸችበት የማንነቷ እና የፍላጎቷ ማደሪያ የሆነ ዐይን ነው። ነገረ ጾታ የተቀበለችውን ነገር በአካሏ ላይ የምታሳይ ከሆነ ሰውነቷ ምርጫዋ ሆነ ማለት ነው ይላሉ እንስታዊያን። ስለዚህ ግጥም ላይ ያለችው ገጸ ሴት በአካሏ ላይ ፍላጎቷን እንድታሳይ ተደርጋ የተሳለች ሴት ትመስል እንጂ ሴትነት ግን አማላይነትን ማሟላት ያለበት ማነነት ነው ተብሎ በእንስታዊያን ተቀባይነት አይሰጠውም። ምክንያቱ ይህ ልማድ እንስቶችን እንስት ላማድረግ አካሏ አማላይ መሆን እንዳለበት የሚያምነውን የልማድ አለም ስርዓት የሚያሳይና ስርዓቱ የሚያስቀጥል ነው።

የገላሽን ማማር የሰራ አካልሽን

የዐይን አገላለጥሽ አሰባበርሽን

እንዲህ ውብ ተፈጥሮን የታደለ ማነው

ዓይንሽን አልሰለችህ አለኝ ባየው (ቴዎድሮስ ካሳሁን፣2012)

በዚህ ግጥም ውስጥ ያለች ሴት በማህበረሰቡ ልማድ ሴት ልታሟላ ያላትን መስፈርት የሚያስቀጥል እንጂ ሁሉንም ዓይነት ሴቶች ባላቸው ጾታው ማንነት የሚቀበል አይደለም።ይህ አፍቃሪ ገጸ ሰብ እንስቷን ምሽቱን አብራው አንድታሳልፍ ይጥቃታል። ከእሷ ጋር ለመሆን አንድ ቀን ብቻ እናዳለው ይናገራል። ሌሊቱን እንጂ ቀኑን እንደማያገኛት እና ዐይኗን ትኩረቱ ነው። ሊሰለቸው የማይችለው የአካል ክፍሏም ዓይኗ ነው። አብሯት ሊያሳልፈው የመረጠው ጊዜ እና የወደደው የሰውነት ክፍል ዓይኗ ከወረት ፍቅር ጋር የተገናኘ እንደሆን ያሳያል።

ከነጋማ ወዲያ ፀሐይ ከደመቀ

ምንም ሳላወጋሽ ሌሊቱ ካለቀ

ኋላ ብትናፍቂኝ ተጠያቂው ማነው

አይንሽ ቀን ከሌት አልሰለችህ አለኝ ባየው (አበበ ብረሃኔ፣2012)

አንድ እንስት መልካም ለመሆን በራሷ ብቻ ሳይሆን በአስተዳደግ እንደምትቀናበር እሙን ነው፡፡ ይህንንም የመጀመሪያው ስንኝ ያሳያል፡፡ ውጫዊ ውበቷ ደግም በፈጣሪ የሚሰጣት ነው፡፡ በዚህ ግጥም ውስጥ ስነምግባሯም ሆነ ውጫዊ ውበቷ የተሟለ እንሰት ወንዱ በጉልበቱ ጠልፎ የራሱ ለማድረግ እንደሚመኛት ሆና ቀርባለች፡፡ በመልካም ምግባሯ እና ውበቷ ምሉዕ የሆነች እንስት ያለፈቃዷ ለመወሰድ በወንዱው አለም እንደተማከሩባት ተገልጧል፡፡ ይህም በስነምግባርም በውበትም የተሟላች እንስት ለሚመርጠው ልማዳዊ ወንድ ንብረት የመሆን እድሏን ከፍ እንደሚያደርገው ይተርካል፡፡

“ፀባዩን ተውሳ ከእናትና አባቷ

እዩኝ እዩኝ ሳትል ደምቃለች ልጅቷ

ግርማ ከሞገሱ እሱም አድሏት

ስንቱ ለጠለፋ ተማከረባት (ሰለሞን አምባው፣2010)

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያ

### 4.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ‹‹ሴትነት በተመረጡ የዘፈን ግጥሞች›› በሚል ርዕስ የተካሄደ ሲሆን በታላሚ የንሞና ዘዴ በተመረጡ ስድስት አልበሞች ውስጥ በሚገኙ የስምንት ወንዶች ገጣሚያን 12 ግጥሞችን ይዘት በእንስታዊያን ንድፈ ሐሳብ ተንትኗል፡፡

ጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ሴትነት እንዴት ቀረበ? በግጥሞቹ ውስጥ የሴት ልጅ ውስጣዊ ገጽታ ምንድን ነው? የሴት ልጅ ውጫዊ (አካላዊ) መልክስ? እና በተተነተኑ የተለያዩ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ ስለሴት ተደጋግሞ የቀረበው ጉዳይ ምንድን ነው? የሚሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች መልሷል፡፡

ትንተናውም የሴት ልጅ ውስጣዊ ገጽታ እና ውጫዊ (አካላዊ) መልክ በሚል ተሸንሽኖ ቀርቧል፡፡

ጥናቱ ባተኮረበት ዘመን በወንድ የዘፈን ግጥም የተገጠሙ ግጥሞች በልማድ ተቃኝተው የወጡ፣ ሚዛናዊነታቸው የተዛባ እና ሴቶችን አሁንም በባህላዊ መንገድ እንጂ በማንነተቻው እንዳልተቀበሏቸው አመላክተዋል፡፡

ከተተነተኑ 12 ግጥሞች ውስጥ አምስቱ ሴትነትን በማንነታቸው ለመግለፅ ጭላንጭል ቢያሳዩም መልሰው ሴትን የወንድ ተከታይ በሚያደርገው ልማዳዊ ዕይታ አደብዝዘዋቸዋል፡፡

በዚህም መሰረት ብስራት ሱራፌል በ2010 ካሳተመው ‹‹ቃልበቃል›› አልበም ውስጥ የሰለሞን አምባው ግጥም የሆነው ‹‹ወይንዬ›› ዐይን የፍላጎቷ ማንጸባረቂያ እና የፍለጎቷ ማደሪያ ሳይሆን የአዲስ ዕይታ መከሰቻ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ቴዎድሮስ ካሳሁን በ2010 ካሳተመው ‹‹ኢትዮጵያ›› ከሚለው አልበም ውስጥ የራሱ ድርሰት በሆነው ‹‹መማጸኔ›› ሴት አታላይ እና የወንድን ሕይወት የምታጨልም ሆና ቀርባለች፡፡ በ ‹‹ያምራል›› ውስጥም ቅንድብን እንደ ሴት ልጅ ልዩ አካል አሳይቷል፡፡

እሱባለው ይታየው በ2010 ካሳተመው ‹‹ትርታዬ›› አልበም የራሱ ግጥም በሆነው ‹‹ማሬማሬ›› ውስጥ ሴትን ልጅ ከልማድ አፋትቶ በራሷ ማንነት መቅረጽ አልቻለም፡፡ እንዲሁም በዚሁ

አልበም ውስጥ በሚገኘው ‹‹ሳምናት›› ዘፈን ሴት እንደሰው ለጥያቄዋ መልስ ፍለጋ በምርጫዋ ወደ ደምትፈልገው መሄዷ ከሃዲ አስብሏታል፡፡

እንዲሁም ዳዊት ጽጌ በ2012 ካሳተመው ‹‹የኔዜማ›› አልበም የአበበ ብርሃኔ እና የናትናኤል ጌታቸው የጋራ ድርሰት ‹‹ደሣለኝ››፣ የቴዎድሮስ ካሳሁን ግጥም የሆነው ‹‹ባየውባየው››፣ ጎሳዬ ቀለሙ በ2011 ካሳተመው ‹‹ባላምባራስ›› አልበም የቢኒያም እሸቱ እና የፀጋው ተክሉ የጋራ ግጥም ‹‹ቀዳማዊት›› ሴት ልጅ በወንድ ፈቃድ ከፍ እንደምትል ሳይፈቅድላት ሲቀር ወደኋላ እንደምትጎተት ሆናለች፡፡ በዚህም የወንድ የበላይነት እንጂ ሴት በራሷ እግር እና እሳቤ ስትቆም አልታየችም፡፡ የቢኒያም መስፍን እና ኤሊያስ ግዛቸው የጋራ ድርሰት የሆነው ‹‹ኖረሻል እንዴ›› የማህበረሰቡን የስህተትና የትክክል መርህ ተከትላ የኖረች፣ የራሷ ማንነት የሌላትን ሴት፣ ጎሳዬ ተስፋዬ በ2012 ካሳተመው ‹‹ሲያምሽ ያመኛል›› አልበም ውስጥ የዓለማየሁ ደመቀ ድርሰት የሆነው ‹‹ከእሁድ እስከ እሁድ›› ሴትን ከምታከናውነው እና ከማንነቷ ትርጉም በማውጣት ሁል ጊዜ በአባታዊው ባህልና ወግ ታስራ የምትኖር የአባታዊውን አለም ስርዓት የሚያስቀጥል ማንነት ያላት እንስት ተበረታትታለች፡፡ የጎሳዬ ግጥም በሆነው ‹‹ተረጋጋሽ ወይ›› ውስጥ ደግሞ በዝምታዋና እርጋታዋ መልካምነትን ማህበረሰቡ የሚሰጣት የራሷ መብትና ፈቃድ የሌላት ሴት አለች፡፡

ከውበት አንጻር የሴትን ውበት ለመግለጽ ቋንቋ ሐሳብን መግለጽ ሲሳነው (በ ማሬማሬ)፣ የሴት ውበት የወንድ ንብረት መሆኑን (በ ወይንዬ) አስረጂነት ማየት ተችሏል፡፡ የሴት ልጅ ልዩ የውበት መከሰቻ ቅንድብ መሆኑን (በ ያምራል) በሌላ በኩል ደግሞ የሴት ውበትና ማንነት ማሳያ ከንፈር ስለመሆኑ (በ እዩዋት) ተጠቅሷል፡፡ ይህም የሴት ውበት መገለጫ ስምምነት እንጂ እውነታ አይደለም የሚለውን የእንስታዊያን ማቀንቀኛ ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱ በሚያቅፈው ዘመን ውስጥ ሴትነት ከማህበረባህሉ እና ማህበረባህሉ ከፈጠራት ውጪ በራሳቸው መንገድ በመጓዛቸው እና ከአባዊው ስርዓት ውጪ በመኖራቸው በግጥም ውስጥ በወንዱ ገጸ ሰብ ውበቷ ከተለምዷዊው የሴት ልጅ ውበት ማወደሻ የተወደሱ፣ በአዲስ አስተሳሰብ በሴትናቷ የተደነቁ ገጸ ሴቶች ተስተውለዋል፡፡

የሴትን አካል ፍረጃ በተመለከተ ቅንድብ፣ ከንፈር እና ዐይንን ወንድን የሚስቡ የሴትነት ማሳይ በማድረግ አካል የማንነት ማደሪያ ብቻ ሳይሆን እንደማንነት ተቆጥሮ ተገኝቷል፡፡ የሴትን አካል አስመልክተው ግጥም ውስጥ የተተረኩት እንስት ገጸሰቦች በወንዶች የተሳሉበት መንገድ አብዛኛው ዐይን እና ከንፍር ተኮር ሆነዋል፡፡

የሴት ውስጣዊ ገጽታን በተመለከተ ሴቶች የሰናይ ባህሪ ባለቤት ለመባል ማህበረባህሉ ባዘጋጀላቸው መመዘኛ መሰረት የሚሄዱት ተንከባካቢ፣ የወንዱውን አለም ጉድለት መሙላት እንደሆነ እና በአሉታዊው ልማዳዊ እይታ ሚዛን ተመዝነው በምርጫቸው ጠወደዱት ጋር ስሄዱ አታላይ፣ ከሃዲ፣ ተደርገው የተሳሉበት እና ከስነምግባር አንጻር በሶሰት ግጥም ውስጥ በራሳቸው አዲስ ማንነት የሚሄዱ ከልማድ ቀድመው የወጡ አዲስ ማንነት ያላቸው ሴቶችን እንደ ጥሩ ሰብዕና ባለቤት ተቀባይነት ሲያገኙ ተስተውሏል ፡፡

***ይሁንታ***

እንስታዊነት በሥነ-ሑፍ ውስጥ በተገቢው ማንነቷ ሳይሆን ሴት ወይም ወንድ ተብሎ በአባውያኑ በተተከለው መረዳትመግለጽ አግባብ አይደለም፡፡ ዘመኑን የዋጀ አረዳድና ገለጻ ያስፈልጋል፡፡

- ሴቶች ያላቸውን የማሰላሰል፣ የመፈጸም፣ የመመርመርና የማወቅ ፍላጎትና አቅም በመመርኮዝ ወንድ ገጣሚያን በሥራቸው ማሳየትና ወደዚህ ንቃት መምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- አታላይነት፣ ከሃዲነት፣ አሳሳችነት፣ አማላይነት የእንስት መገለጫ አይደሉም፡፡ እነዚህ ድርጊቶች የማንኛውም ሰው እንጂ የአንድ ጾታ ጣጣ አለመሆናቸውንም ማሳየት ይገባል፡፡

## ሀ. ቀዳማይ የመረጃ መምንጮ


ብስራት ሱራፌል፡፡ *ቃል በቃል፡፡* አሳታሚ እና አከፋፋይ፣ ሆፐ ኢንተርቴመንት፣ 2010፡፡

ቴዎድሮስ ካሳ፡፡ *ኢትዮጵያ፡፡* አሳታሚ እና አከፋፋይ፣ማንኩሳ ኢንተርቴመንት፣ 2010፡፡

እሱባለው ይታየው፡፡ *ትርታዬ፡፡* አሳታሚ እና አከፋፋይ፣ ምነው ሸዋ ኢንተርቴመንተ፣ 2010፡፡

ዳዊት ጽጌ፡፡ *የኔ ዜማ፡፡* አሳታሚ እና አከፋፋይ፣ ባለ ሀገሩ ቴሌቭዥን፣ 2012፡፡

ጎሳዬ ቀለሙ፡፡ *ባላምባራስ፡፡* አሳታሚ እና አከፋፋይ፣ ጎሳዬ ቀለሙ፣2010፡፡

ጎሳዬ ተስፋዬ፡፡ *ሲያምሽ ያመኛል፡፡* አሳታሚ እና አከፋፋይ፣ ጎሳዬ ተስፋዬ፣ 2011፡፡

## ለ. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች


መላኩ ጌታቸው። ‹‹የእጅጋየሁ ሽባባው የዘፈን ግጥም ይዘት ትንተና››። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ሚካያ በኃይሉ። ‹‹የውስጣዊ ሰብዕና አቀራረጽ በሶስና ታደሰ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ››። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 1996።

Brown L. Cheryl and Karen Olson. (eds.). *Feminist Criticisms Essayes on Theory, Poetry and* Proso, New York; The scarecrow Press 1978.

Judith Butler *Sex and Gender in Simone de Beauvoir's Second Sex*, French, Yale University Press, 2021.

Feorgusor Mary Anne. Image of Image of women in Literature.(2nd ed). 1977 (1973)

Humm,Maggie *FeministLiterary Thyeory In contemporary feminist theories.* Stevi Jacksor and Jacki Jones(eds.)Edinburgh: Edinburgh univerdity perss,194-212,1998.

Kowaleski, Elizabeth. (ed). *Encycolopedia of Feminist Literart Theory*; Wallace Garland Publishing Inc, 1997.

Ruth, Sheila. *Issues in Feminism (An introduction to women's studies)*, Mountain view California; May Field Publishing Company. 1995.

Tyson,Lois. Critical Theory today:A user —Friendly Guide.(2nd end).new York: Routledge,2006(1999).

Neguss Yilma. ‹‹Thematic Analysis of Selected Amaharic Song Lyrics: A sociological Approach››. Addis Ababa Univesrsity, Fulfillmente of Doctors of Philosophy in Literature, Departemenet of Foreign Language and Literature, 2018.

Wube kassaye. ‹‹Content analysis of a secular Amaharic songs Produced in cassettes (1974-1994), Addis Ababa University, Fulfillmente of Masters, Departemenet of Education Implications for curriculum planning, 1995.

## አባሪ

**ትራክ 8 ‹‹ጎዳና ሙሉ›› እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

**ድርሰት፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

ተመርጦ ለንግስ እንደበቃ

የስቃይ ሎሌነት አበቃ

በፍቅር ነገስኩ

ትልመቴን ረገጥኩ

ሆነሻል ብርታቴ

የእናት ቃል ዕወቀቴ

ጎዳና ሙሉ ዋለ ጎዳና ሙሉ ደስታ

ጎዳና ሙሉ ፈኼታ

ጎዳና ግራ ቀኜ አንቺን ይገፎ ሳለፋ

ተሞላልኝ በተስፋ

መላው እኔነቴ አደረገኝ

ስም አልባ ደስታ ከበበኝ

አሮጌውን አድሰሻል

የእድሜ ጀንበር ያንስሻል

ተመርጦ ለንግስ እንደበቃ

የስቃይ ሎሌነት አበቃ

በፍቅር ነገስኩ

ትልመቴን ረገጥኩ

ሆንሽልኝ ብርታቴ

የእናት ቃል ብርታቴ

ጎዳናው የእኔ አለም

እንደ አዲስ ተሰላ ትላንት ዛሬ የታለ

በፍቅርሽ ያለው ተረሳ

የመኖር ጉጉቴ ተረሳ

አሮጌውን አድሰሻል

የእድሜዬን ድንበር አንግተሻል

መወደድ ያንስሻል

መወደስ ያንስሻል

**ትራክ 13 ‹‹ሳምናት›› እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

**ድርሰት፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

ሳምናት ሳምናትሳምናት

ምን ሆንነ ነህ ነው የከፋህ ይላሉ

የተጨነክ

ሳለቅስ …ሳነባ ስተክዝ መዋሌን አላዩ

ላላ…ላ…ላ

ሂ…ሂ …ሂ

ህልም  ቅዠት የውሸት መስሎኝ

መሄዷን ማመን ተስኖኝ ነው እንዴማልነቃ

የገባኝ መሄድ መራቋ

ገልጻ ሳትነግርኝ ጥፋቴን

አውጥታ ጣለቸው እምነቴን

ለሰሚው ግራ ነው የሷ

ሳምናት የከዳኝ ልቧ

ግልግል ያውቃል አውቃለሁ

ያልደረሰበት ችግር

በራስ ሲደርስ ነው እንጂ

አሳር የሚያሳይ ፍቅር

ሳምናት ነው የከዳችኝ ሳምናት

ስወዳት ነው የሄደች ስወዳት

ሳምናት ነው የከዳችኝ ሳምናት

ሰው አምኜ መከዳቴ

ብታሳየኝ የእውነት ዕዳ

ሳምናት ነው የከዳችኝ ሳምናት

ስወዳት ነው የሄደች ስወዳት

ሳምናት ነው የከዳችኝ ሳምናት

ሳምናት

ሳምናት

ሳምናይ

**ትራክ 14 ‹‹ማሬ ማሬ›› እሱባለው ይታየው (የሺ)**

**ደራሲ፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

ምሳሌ አምሳል ምን አለ ላንቺማ

ላረግሽው  ምግባር ከቶ ሚስማማ

ቢመነዘርም በዐለም ካለሁ

አንቺነትሽን ለእኔ አይገልጸውም

አይገልፅውም x 4

ያንስብኛል ይሳሳል ለእኔ

ሆሄ ፊደላት ሰዋሰው ቅኔ

ውበት ቁንጅናሽ በምን ይለካ

በማን ጠርቼሽ ምን ብዬ ልርካ

ማሬ ማሬ ማሬ ማሬ

እንደው ነፍስ ነገር ነሽ ለእኔ

ውቤ ውቤ ውቤ ውቤ

እንደው ነፍስ ነገር ነሽ ለእኔ

ቀንቶኝ ዕድሌ በስም በተራ

በፍቅርሽ ብርሃን  ቀኔ ሲበራ

ማሞገሻ ቃል ላገኝ ብለፋ

ፊልጌ አጣሁኝ ስያሜሽ ጠፋ

ማሬ ማሬ ማሬ ማሬ

እንደው ነፍስ ነገር ለእኔ

ውቤ ውቤ ውቤ ውቤ

እንደው ነፍስ ነገር ለዐይኔ

እፍኝ ማይሟላ

ዕድሜዬ በዝቶ

ዜማው አምሮልኝ

በአንቺ ተቃኝቶ

መንገዴ ቀና ሕይወቴ ሙሉ

አንቺ ካለሽኝ ተድላ ነው ሁሉ

ማሬ ማሬ ማሬ ማሬ

እንደው ነፍስ ነገር ለእኔ

ውቤ ውቤ ውቤ ውቤ

እንደው ነፍስ ነገር ለዐይኔ

በአንቺ ሁሉ አለኝ አለኝ ደስ ደስ

እንግዳ ሆነኩኝ ለአለም እንደ አዲስ

ብቸኝነቴ በአንቺ ኮንኜ

በፍቅር ልቁ ቆምኩኝ ሰው ሆኜ

ማሬ ማሬ ማሬ ማሬ

እንደው ነፍስ ነገር ለእኔ

ውቤ ውቤ ውቤ ውቤ

እንደው ነፍስ ነገር ለዐይኔ

**ትራክ 4 ‹‹ትርታዬ›› እሱባለው ይታየው (የሺ)**

**ድርሰት፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

ትር ጸሐይ ነሽ

ትር ብርሃን(ትር)

ትር ጸሐዬ

ትር ለእኔ(ትር)

ትር ለልቤ(ትር)

ትር ሰማይ…

አሃ…ደስታ የሚከብኝ(አሃ)

በፈገግታሽ(አሃ)

የልቤ አንድ ምት

ትርታዬ ነሽ

ትር ትር ትርታዬ 2x

የልቤ አንድ ምት አንቺ ነሽ ብርታቴ

ትር ትር ትርታዬ 2x

የልቤ አንድ ምት አንቺ ነሽ ብርታቴ

ኡህ…ኡህ ብዬ

እንደ ማለዳ የወፍ ዜማ

አ…አ..አለሜ

አልጠግብም ድምጽሽን ብሰማ

ኡህ…ኡህ …ብዬ

እንደ ሎሚ ሽታ ጠረንሽ

ኣ..ኣ…አለሜን

መልካም መዓዛ ነው መለያሽ

ኡህ…ኡህ …ብዬ

እንደ ውብ አበባ በዐይኖቼ

ኣ..ኣ…አለሜን

መቼ እሰለችና አይቼ

ኣ..ኣ…አለሜን

አቧራ ሳሩ ይሰክናል

ደረቅ ሳሩም ይለመልማል

የዋልሽት ሁሉ ይለያል

ፍቅር ነሽ ባንቺ ማን ይጨክናል

ትር…ትር ትርታዬ

የልቤ አንድ አምት አንች ነሽ ብርታቴ

ኡህ…ኡህ …ብዬ

ጥቂቱን ዘርቼ ብዙ አፈስኩ

ኣ..ኣ…አለሜን

በፍቅርሽ ፍቅርን አተረፍኩ

ኡህ…ኡህ …ብዬ

ደስታዬ ልክ ያጣል ወሰን

ኣ..ኣ…አለሜን

ሳገኘሽ ጥርሴ አይከደን

ኡህ…ኡህ …ብዬ

የቀረሽ ያጣሁሽ ዕለት

ኣ..ኣ…አለሜን

ልክም አይሆን የልቤ ምት

ኣ..ኣ..ኣ…አሄ

ኣ..ኣ..ኣ…አሄ

ኣ..ኣ..ኣ…አሄ

አቧራ ሳሩ ይሰክናል

ደረቅ ሳሩም ይለመልማል

የዋልሽት ሁሉ ይለያል

ፍቅር ነሽ ማን ባንቺ ይጨክናል

ትር…ትር ትርታዬ

የልቤ አንድ አምት አንች ነሽ ብርታቴተ

**ትራክ 5 ‹‹ከአይኔ አትጠፊም›› እሱባለው ይታየው (የሺ)**

እንደ እህል እንደ ውሃ

ይርባል ይጠማል

ጨዋታሽስ  ይቅር

ኩርፊያሽ ይናፈቃል

እንኳን ካጠገቤ ከጎኔ ርቀሽ

አላውቅም ጠግቤ ዐይኔ ስር ሆነሽ

እልፍ ቢሆን ጓዙ የትዝታሽ ዐይነት

ቢበረታ ውጊያው ቢታገለኝ ናፍቆት

እንደ መሃረቧ እንደናቴ ሙዳይ

አስቀምጬሻለሁ በልቤ ሳላሳይ

ከአውራ ጎዳናው ከተጓዝንበት ካረፍንበት

ሳልፍ ሳገድም ዕንባይ ይፈሳል እንደዘበት

አይጠፋም ከዐይኔ ቁምነገር ለዛ ያለሽ ውበት

አንዳች ቀን የለም ያንን ውብ ጊዜ የምረሳበት

ከዓይን አይጠፋም ሁሌ ሁሌ 2x

አንቺ አካል የእኔ

**ትራክ 6 ‹‹እንደ ወይን›› እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

**ድርሰት፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

እንዳ አዲስ ሲቆይ ጣእም ከርሞ የሚጨምር

እንደ ወይን ሆነብኝ ዘውተር ልዩ የአንቺስ ፍቅር

እንደወይን ተወዳጅ ነሽ በቀን በቀን

እንደወይን ጣእምሽ ልዩ በቀን በቀን

የጥፍጥናው ሚስጥሩ መቆየቱ ጊዜው በሄደ ቁጥር መፈለጉ

አመታት ሲጨምር ነው ጣዕም ቀን በቀን

መወደዱ የወይን ወጉ

እኔስ  ሁለት አዲስ ጊዜው  ሲርቅ አዲስ

እንደ ወይን ሆነብኝ የእኔ እና ያንቺ መውደድ

ተመኘው በድንቅ ፍቅር ሳፈቅርሽ ልኑር አብሬ

እድሜ ማምሻ ድረስ ጉም እስኪመስል ጸጉሬ

እንደወይን ተወዳጅ ነሽ በቀን በቀን

እንደ ወይን ጣእምሽ ልዩ በቀን በቀን

እንደወይን ተወዳጅ ነሽ በቀን በቀን

እንደ ወይን ጣእምሽ ልዩ በቀን በቀን

አንቺ ወይኔ ይህ ማድጋሽ

ፍቅርን ማስቀመጫ ማደሪያሽ

ጣዕም አልባ ወና ውስጠቴን ደረስ

በደስታ በሀሴት የሞላሽ

ቀን በቀን አዲስ  በጉጉት የማገኝሽ

ሁሌም ተናፋቂ ሁል ጊዜ ልዩ ነሽ

ተመኘው በድንቅስ ፍቅር ሳፈቅርሽ ልኑር አብሬ

እድሜ ማምሻ ድረስ ጉም እስኪመስል ጸጉሬ

እንደወይን ተወዳጅ ነሽ በቀን በቀን

እንደ ወይን ጣእምሽ ልዩ በቀን በቀን

እንደወይን ተወዳጅ ነሽ በቀን በቀን

እንደ ወይን ጣእምሽ ልዩ በቀን በቀን

**ትራክ 2 ‹‹የትም ይመቸኛል›› እሱባለው ይታየው (የሺ)**

**ድርሰት፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

ወዬ …ወይ…ወዬ 2x

ብቻንቺ ኑሪል3x እንጂ 2x

የትም ይመቸኛል የትም 2x

ወዬ …ወይ…ወዬ

ውብ ባይሆን ስፍራው ለዐይን ባያምር

ካለሽ ይደምቃል(ካለሽ ይደምቃል)

ከፍ ያለ ቦታ አንቺ ከሌለሽ አንሶ ዝቅ ይላል(አንሶ ዝቅ ይላል)

ሳትኖሪ ቀርተሽ ደስታም ደስ አይለው ደርሶ ይከፋል

አንቺ ካለሽ መጨነቅ እንኳን ጨንቆት ይሞታል

ባለሽ ቦታ ላይ ብትወስጂኝ2x (የትም)

ኖረሽ ደስታ እንጂ ከፍቶኝ አያውቅም 2x

የትም ይመቸኛል 4x

ወዬ …ወይ…ወዬ

ወዬ …ወይ…ወዬ

ብቻንቺ ኑሪል3x  እንጂ 2x

የትም ይመቸኛል የትም 2x

ወዬ …ወይ…ወዬ

አጊኝቶሽ ማነው በዋዛ ካንቺ መለየት ሚፈቅድ (መለየት ሚወድ)

ጫዋታ ለዛ ቁምነገርሽ አድርጎት ሚወደድ(አድርጎት ሚወደድ)

ላለ መደሰት የማለ ካለ

ፊትሽ ያስታል የቃልሽ ማማር ሁሌ ካንቺ ጋር መሆን ያስመኛል

ባሻሽ ቦታ ላይ ብትወስጂኝ የትም2x

ኖረሽ ደስታ እንጂ ከፍቶኝ አያውቅም

የትም ይመቸኛል የትም4x

ወዬ …ወይ…ወዬ

ወዬ …ወይ…ወዬ

**ትራክ 3 ‹‹ደግሞ ደግሞ›› እሱባለው ይታየው (የሺ)**

**ድርሰት፡- እሱባለው ይታየው ይታየው (የሺ)**

ስለ አንቺ ቢነግረኝም

ልለይሽ ፈጽሞ አልቻልኩም

እንዳልቀርጥ አቃተኝ እንዳልቀርጥ

ከሰው አላየሁሽ እንዳልቆርጥ

ደግም ይታየኛል ውበትሽ

ሳስብ ልለይሽ

ደግሞ ደግሞ ይመጣና ያፈገግታሽ

ድቅን ይላል ሳቅሽ

ትሄጃለሽ ይሉኛል ወዳጅ አፍርተሽ ሌላ

ቤት ምስላችን ሳይፈርስ

ማህተባችን ሳይላላ

እንደምን ብዬ ልመን

ምንስ ሰበብ አገኝቼ

አላጎደልሽብኝም እንዴት ልጥላሽ ሰምቼ

እንዳልቀርጥ አቃተኝ እንዳልቀርጥ

ከሰው አላየሁሽ እንዳልቆርጥ

ደግም ይታየኛል ውበትሽ

ሳስብ ልለይሽ

ደግሞ ደግሞ ይመጣና ያፈገግታሽ

ድቅን ይላል ሳቅሽ

ደግሞ ደግም ያታየኛል ውበትሽ

ሳስብ ልልይሽ

ደግም ደግሞ ይመጣና ያፈገግታሽ ድቅን ይላል ሳቅሽ

ውበቱ እስኪ ምንድነው

ቤቱ ያላንቺ ፍቅር

ሆኖለትስ ረስቶሽ ልቤ ይችላል ወይ መኖር

ብሮጥ እንኳን አላመልጥ

እንደ ንስር በርሬ

ሁሉ ቦታዬ አንቺው ነሽ

ሆነሻል ሰማይ ምድሬ

እንዳልቆርጥ አቃተኝ እንዳልቆርት

ከሰው አላየሁሽ እንዳልቆርጥ

ደግም ደግሞ ያታየኛል ውበትሽ

ሳስብ ልለይሽ

ደግሞ ደግሞ ይመጣና ያፈገግታሽ

ድቅን ይላል ሳቅሽ

**ትራክ 1 ብስራት ሱራፌል ‹‹አትንኳት››**

**ድርሰት፡-ሰለሞን አምባው**

ሉ ላላ ሉሉ ላላ (3)

ያች እርግብ የዋህ ናት አንጀት የምትበላ

ትርፍ ክንፍ የላትም አትንኳት በባላ

ፀባይዋ ፍቅር ነው አመሏ ዝምታ

ያኔ እኔን አያርገኝ ሰው የነካት ለታ

ሉ ላላ  ሉሉ ላላ

ትመላለስ ባይኖቼ ትውረድ በልቤ ሰማይ

ውዬ ማደር አልችልም ሰላም መሆኗን ሳላይ

ላላምዳት እንጂ አቅርቤ ትረፍ በልቤ ገብታ

መቼም ጠላፊ አይጠፋ ተውባ እንዲህ ቆንጅታ

ለኔ እሷ ገዴ የእድሌ መገኛ

የነኩብኝ እንደው ከልካይ የለ ዳኛ (2)

"ፀባዩን ተውሳ ከእናትና አባቷ

እዩኝ እዩኝ ሳትል ደምቃለች ልጅቷ

ግርማ ከሞገሱ እሱም አድሏት

ስንቱ ለጠለፋ ተማከረባት

እያዩ ነው ማለፍ አለ ብሎ ብስራት

ነገር እንዳይመጣ ባላ ተሰርቶባት

ይቀስሙታል እንጂ ቆንጆን እንደ አበባ

እንዴት ይሰደዳል ወንጭፍና ባላ

እኔም ይሄንን ሳይ ቀረሁ ከመንገዴ

ብለው የዘፈኑት ለዚሁ ነው እንዴ

እኔም ቀርቻለሁ ከመንገዴ እንዳልኩሽ

የወዳጄ ወዳጅ ሆነሽ በመምጣትሽ"

ሉ ላላ ሉሉ ላላ (3)

ስናገር ስለዋለሁ ደግሜ ደጋግሜ

ለእንስፍስፍ የዋህ ልቧ አለሁለት ዘብ ቆሜ

ሰው አለሽ እኔን መሳይ በመውድሽ ሚኩራራ

ስጠብቅሽ በምነቴ አንቺ ፍቅሬን አደራ

**ትራክ 2 ብስራት ሱራፌል ‹‹ወይንዬ››**

**ድርሰት፡- ሰለሞን አምባው**

. ተገኘሽ ከላይ እንደ ደመና ወይንይዬ በቁንጅና

አድናቆት ብቻ አይበቃሽም ቆንጆ ነሽ አልተውሽም

ኧኸ አይንሽን ለጥቅሻ ኧኸ ከንፈርሽን ለቅምሻ ኧኸ

አየሁት በስስት መንገዴን እስክስት ኧኸኸ

ኧኸ ውብ አርጎ ቢሰራሽ ኧኸ ፈጣሪ ባምሳሉ ኧኸ

ትወዛወዘልሽ ያየሽ ሳር ቅጠሉ ኧኸኸ

ሰው አለኝ አምላኬ ከሰውም የክት

ተቀምጠሽ ብርሃን ቆመሽ መስታወት

ስከተልሽ  አንቺን ከልብሽ ስጠጋ

ታፈርኩኝ እንደባለፀጋ

ይኸው ሆነች እድል ከኔ

የልቤ ሰው አርጓት ጎኔ

የኔ አረጋት የኔ ብቻ

ወይኗ የኔ እኔም የሷ ብቻ

ወይንዬ ወይኗ ነይ ወይንዬ ወይኗ ነይ(3)

አዝ

እንደ ምኩራብ ደውል ነው ለነብስያዬ

ቃልሽ ዘለሰኛ ድምፅሽ መዲናዬ

እህ ስልሽ ኑሪ ነግሰሽ በላዬ ላይ

ፈሰሽ እንደ ክረምት ሞቀሽ እንደ ፀሐይ

**ትራክ 3 ብስራት ሱራፌል ‹‹እዩዋት››**

**ድርሰት፡- ናትናኤል ግርማቸው**

ይሰማኛል ደስታ ከሌሎች አብልጣ

ኮራ እያለች ወደኔ ስትመጣ

አታምርም ወይ ታዲያ የእውነት እዩዋታ

ገና ከሩቅ በአይኖቿ ምትረታ

እዩዋት የልቤ ብዬ ያልኳችሁ እዩዋት የማጫውታችሁ

እዩዋት እኔን ብላ ተገኝታለች ተመልከቷት ያው መጥታለች (2)

ከውበት ከመልክሽ በላይ ቁምነገረኛ አስተዋይ

በአስተሳሰብሽ ምትሀት ያንሰኛል ወይ መረታት

ቁንጅና ማለት እንደዚ ነው

የለም ስለኔ የማትሆነው

ቅን አሳቢ ናት ደግ መልካም

በሌላ አትተካም

ቁንጅና ማለት እንደዚ  ነው

የለም ስለኔ የማትሆነው

በቀን በፀሐይ በጨረቃ

ደስተኛ ናት በቃ

አዝ

ተወዳጅ ናት ፍቅር አዋቂ

የኔን ደስታ ናፋቂ

ሰላም ሰጠኝ ለዘመኔ

ካንቺ ጋራ መሆኔ (2)

**ትራክ 4 ብስራት ሱራፌል ‹‹የቤት ስራ››**

**ድርሰት፡-ናትናኤል ግርማቸው**

አሄ እኔ ቀናተኛ አሄ እሷ ስንቱን ወዳጅ

ታድያ እንዴት ባንድ ይውላል ታድያ ክብሪት እና ነዳጅ

ጉድ ነው ደሞ አዲስ አመጣች  አሄ ሳልፈው ሁሉን ችዬ

አቤት እንደው የቤት ስራ ምንው ሆንሽብኝ አንቺዬ

ሆንሽብኝ የቤት ስራ የቤት ስራ (4)

አልፈናት ነበረ እችን እችንማ

አይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማ

ፍቅርን በቁም ነገር አቅቶሽ መገንዘብ

የትም የትም በታተንሽው እንደ ጠላት ገንዘብ

አዝ

ግራ ስልሽ በቀኝ ቀኝ ስልሽ ግራ

ሆነሽ አስቸገርሽኝ ከባድ የቤት ስራ

ፍቅርን በቁም ነገር አቅቶሽ መገንዘብ

የትም የትም በታተንሽው እንደጠላት ገንዘብ

**ትራክ 1 ጎሳዬ ተስፋዬ ‹‹ከእሁድ እስከ እሁድ››**

**ድርሰት፡- አለማየሁ ደመቀ**

ሰው አይጠፋም ቤትሽ ከእሁድ እስከ እሁድ

ዳስ ጥለሽበታል ላንድ ቀን ሳይወርድ

ያላየሽ አይድንም ቀና አይሆንም ቀኑ

የሚል አዋጅ አለ እስኪመስል ሙሉ

አይነጥፍም አይጎልም ማጀትሽ ቢጠጡ ቢበሉ

እስከ እሁድ ሰው እንዲህ መውደድ

እንዴት ብሎ ያንን ሁሉ አባብሎ

ካንድ እሁድ እስከ ሌላ እሁድ

ግብዣ ተያይዟል ፍቅር ካንቺ አፀድ

ከምን አርጎ ይሆን ልብሽን ያነፀው

ለከበበሽ ሁሉ ፍቅር የሚለግሰው

አንቺ የልጅ አዋቂ ልብሽና ቤትሽን የማትደብቂ

ፍቅር ካንቺ አፀድ ዳሱን ጥሎ ይኖራል ከእሁድ እስከ እስከ እሁድ

እስከ እሁድ ሰው እንዲህ መውደድ

እንዴት ብሎ ያንን ሁሉ አባብሎ

ስስት ያልነካካው እስከ እሁድ

ምን እንደሚተካው እስከ እሁድ

ዳር ይደርሳል እጇ እስከ እሁድ

የሁሉም ነው ደጇ እስከ እሁድ

ከእሁድ እስከ እሁድ እኔ እሷን መውደድ

የሚያጠግብ አፀድ ለሁሉም ለጉድ እስከ እሁድ

አዝ

ታላቅና ታናሽ ባይሰፍርም እቤቷ

የሷን ትንሽነት ሰማሁ ከአንደበቷ

ወትሮም ዝቅ ያለ ነው

ካጀብ ተነጥሎ ከፍ የሚለው

አረ ያንቺ ስራ

ቀን ሌሊት ይተጋል ፍቅርን ሲሰራ

**ትራክ 2 ጎሳዬ ተስፋዬ ‹‹ተረጋጋሽ ወይ››**

**ድርሰት፡-ጎሳዬ ተስፋዬ**

. በፍቅር የማትረጋ ሰው ወድጄ

ላልይዛት ላላስቀራት አስገድጄ

ይኸው ስከተላት እኖራለሁ

ጨክኜ እንዳልተዋት ጥሎብኝ ደሞ ወዳታለሁ

ንገሪኝ አረ እንደምን ከርመሽ ይሆን

ከማን ጋር ውለሽ አደርሽ ይሄን ሰሞን

ማነው ባለሳምንት ተረኛሽ

ተረጋግቶ ሊኖር ያሰበ እንደኔ ሚያጣሽ

ያለቀልብ አቡክተው ያበሰሉት ያህል ጠረኑ ቢጠራን

ትርፉ ቃር አይደል መች ሰውነት ሊሆን የገፉት እንጀራ

ላትኖሪበት ነገር አስር ቤት ለመስራት አስሩን ስታይ

የእግዜሩ እንዳይጠፋሽ መብረሩን አቁመሽ ተረጋጋሽ ወይ

ተረጋጋሽ ወይ ተረጋጋሽ ወይ

ነፍስሽ ከስጋሽ ታረቀልሽ ወይ

የለበስሽው ልብስ ያጌጥሽው ጌጥ

ለምን ውድ ሆነ ካንቺ ሳይበልጥ

ምን ውድ ቢሆን ይመነችካል

ጨርቃ ጨርቅ ነው በውሀ ያልቃል

ተረጋጋሽ ወይ ተረጋጋሽ ወይ

አዝ

ለምን አሰርሽው ይሄን ሁሉ ክታብ ይሄን ሁሉ ዋሻ

አራት ክንድ አይደል ወይ የኔና ያንቺ ቤት በስተመጨረሻ

ለማን አቤት ልትይ ስትሮጪ የታጠቅሽው ስትሮጪ ቢላላ

ውሸትሽን ንቆ ይከተል እምነትሽ እንደማምሻ ጥላ

ተረጋጋሽ ወይ ተረጋጋሽ ወይ

ነፍስሽ ከስጋሽ ታረቀልሽ ወይ

አርጊው በርጋታ ሁሉን በቀል

የዘራሽው ነው ነገ ሚበቅል

ያበቀለውን የንባ ጥማድ

ፃድቅ ብቻ ነው በደስታ ሚያጭድ

ፅድቁ ቀርቶብሽ ወጥተሽ ከድጡ

እንዲኮንንሽ  እግዜር በቅጡ

**ትራክ 1 ቴዎድሮስ ካሳሁን ‹‹እማ ዘንድ ይደር››**

**ድርሰት፡- ቴዎድሮስ ካሳሁን**

ማ ዘብ ይደር ሄዶ ጎኔ

ሰው አልሆንም ያላንቺ እኔ

ማ ዘብ ኖሮ ለኔ ገላ

ደሞ አያለሁ ካንቺ ሌላ

ልምጣ ወይ ልቅር ምን ይሻለኛል

ከፍቅርሽ ሚያስጥል ማን ሰው ይገኛል

ስለት አለብኝ ከርቤና እጣን

ለመተያየት እንዲያበቃን

የጠቢቡ ሰው የሊቁን ቅኔ

ህልሜ አይፈታ ሳላይሽ እኔ

ማ ዘብ ይደር ሄዶ ጎኔ

ሰው አልሆንም ያላንቺ እኔ

ማ ዘብ ኖሮ ለኔ ገላ

ደሞ አያለሁ ካንቺ ሌላ

የብራና ስር አይነ ጎላዬ

መልከ ማክዳ ሳባ መሳይ

የሸማሽ ጥለት ቀድሞ ሰንደቄ

ያስታውሰኛል ላንቺ መውደቄ

ልቤ አምሮህ ሌላ ዝቅ አትበል ይቅር

አገር ያህላል ከፍ ያለ ፍቅር

ማ ዘንግ ይዞ ገብቶ ገዳም

ያገናኘው ፍቅርን ካዳም

ማ ፆም ይዞ ቆጥሮ ጠጠር ባሳከለው ፍቅርን ሀገር

ማ ዘብ ይደር እማ ዘብ ይደር(2)

ሰው አሳዝኖ ሰው ላይሆን ነገር

ምን አስጀመረው የማይሆን ነገር

ልቤ አንቺን ትቶ ከማን ዘንድ ይደር

ልማልልሽ ወይ በቶ መስቀሌ

ከራሴ ጋር ነው ብጠላሽ ጥሌ

ማ ዘብ ይደር እማ ዘብ ይደር

ዘቢደር ዘቢደር እማ ዘብ ይደር (2)

ድር አስደርዳሪው ጥልፍ የጠለፈው

አስዋብኩሽ ብሎ ምን አስቆፈረው

ሽማ ዘግይቶ ቀለም ቢነከር

ልብስ አያምርበትም ያ ራቁት ሀገር

ዘብ ይደር ዘብ ይደር እማ ዘብ ይደር

**ትራክ 2 ቴዎድሮስ ካሳሁን ‹‹ማራኪዬ››**

**ድርሰት፡- ቴዎድሮስ ካሳሁን**

በምስራቅ ፀሐይ ወጥቶ እስኪፈታ ሰማይ

ካንሶላው ገብቼ እኔ አልተኛም ብታይ

በናፍቆትሽ እንባ እየራሰ አልጋዬ

ካላንቺ አቅቶኛል ማደር ለብቻዬ

ማራኪዬ ማራኪዬ አንቺ የልቤ ጉዳይ

መልክሽ ሁሌ ባይኔ ላይ ነው ሌትም ቀንም ብታይ (2)

ማርኮ መማር ነበር የጀግና ሞገሱ

ከሩቅ አስረሽ ልቤን የት ያምልጥ ከራሱ

የጎደለው ካርባ ስንት ይሆን እጣዬ

ካላንቺ አልሞ አለኝ እርጂኝ ማራኪዬ

ማር ማር ይላል ሁሌ አፌ ሲጠራሽ

ማር ማር ይላል እያቆላመጠ

ማር ማር ይላል አይኖር ያላንቺ

ማር ማር ይላል እድሜ እየጣፈጠ

መች ጠገብኩሽ እና እኔ ሌት ይድላኝ አልጋዬ

ፍቅርሽ ጠንቶብኛል እኔ አልተኛም ጨርሶ

ማታ ማታ ማልቀስ ነው ስራዬ

አዝ

**ትራክ 3 ቴዎድሮስ ካሳሁን ‹‹ያምራል››**

**ድርሰት፡- ቴዎድሮስ ካሳሁን**

ስፍራ ጠብቆ  ያንቺ ውበት ጎልቶ ቢታይ ፈክቶ እንደ ፀሐይ

ውብ ያደረገሽ ባይንሽ ዙሪያ ቅንድብ ስሎ ኩል አስመስሎ

እንዴት ታምሪያለሽ ውቤ መሳይ ውበትሽ ጎልቶ ለአለም ይታይ

ከከንፈርሽ ላይ ፅጌረዳ ሳይ

ከራሴ ጋራ እስከምለያይ

ብቀር ፈዝዤ ጠፍቶኝ ማረገው

አይኔን ካፍሽ ላይ ጣል ባረገው

ሳማት ሳማት አለኝና ቀልቤን ገዛው እንደገና

ሳሙኝ ሳሙኝ የሚል ከንፈር ድንገት አጉል አርጎኝ ነበር

አልሰማ ቢል ልቤ ውበት ሲጣራ ሲለኝ ና እና እይ ሲለኝ ና እና እይ

መች እለያይ ነበር ከራሴ ጋራ ሲለኝ ና እና እይ ሲለኝ ና እና እይ

ልብ አሸፍቶ ቀልብ ያሰውራል

ቁንጅናሽ ለጉድ ያምራል

ያምራል ያምራል ቁንጅናሽ ያምራል

ያምራል ያምራል ውበትሽ ያምራል

ልቤ ልብ አጣ ቀልቤን ሰወርሽው

መልክሽ ሲጣራ ሲለኝ ና እና እይ

አዝ

የገና ፅድ ጌጥ የሶሪት ናባ

ማን አበቀለሽ አዲስ አበባ

ቀድሞኝ ፈዝዤ ጠፍቶኝ ማረገው

አይኔን ካፍሽ ላይ ጣል ባረገው

ሳማት ሳማት አለኝና ቀልቤን ገዛሁ እንደገና

ሳሙኝ ሳሙኝ የሚል ከንፈር ድንገት አጉል አርጎኝ ነበር

አዝ

**ትራክ 4 ቴዎድሮስ ካሳሁን ‹‹መማፀኔ››**

**ድርሰት፡- ቴዎድሮስ ካሳሁን**

ቀና አታርጉኝ እኔን ከሄደች ጥላው መማፀኔን

ጨለማ አልብሳው ስትሔድ የፈካው ቀኔን

እኔስ አቅም የለኝም እባክሽ ብዬ ልመላሳት

ቢፈጀው እግሬን የፍቅር እሳት

አይሞከርም መቼም እሷን ለመርሳት

ስትሄድ ስለያት አሄ ስሰናበታት

ማን አወቀልኝ ውስጤን እንደምወዳት

ልሸኛት እንጂ የሆዴን ችዬ

ባይል ነው ከላይ ግድ የለም ብዬ

ገና በጊዜ በቀዬው አድባር አብረን አድገን

ክፋት በሌለው በንፁ ፍቅር ተፈላልገን

ተዋደን ኖረን ባልነበር አይነት በሚያስቀና

ልቧን ከልቤ ድንገት ለያዩን ቀን መጣና

በደለኛ ሰው ይቅርታ ብሎ አዝኖ ሰው ከካሰ

ይኖር የለ ወይ ልቡን ያልመለሰ

ሳይገባኝ ለኔ የቱጋ እንደሆነ እንኳ ማስቀየሜ

ተይ ብያት ነበር ባለኝ አቅሜ

መማፀኔ ማሪኝ ማለቴ ለኔስ ሳይገባኝ ነው ጥፋቴ

ታዲያ እንዴት ይሆን ወዳጅን መክሮ

ልብን መመለስ ወደ ድሮ

መማፀኔ ማሪኝ ማለቴ ያውም ሳይገባኝ ነው ጥፋቴ

ታዲያ እንዴት ይሆን ወዳጅን መክሮ

ልብን መመለስ ወደ ድሮ

አዝ

በዚ አለም ሚዛን ደስታ ያለ ፍቅር መች ይሞላል

በሌለሽበት ስኖር ያላንቺ ቀን ይጎላል

እስቲ አምነንበት ሰው ሳንፈልግ ሌላ ዳኛ

ብለን ለፍቅር ተይ እንገናኝ ዞረን እኛ

**ትራክ** 1 **ዳዊት ፅጌ ደስ ‹‹አለኝ››**

**ድርሰት፡- አበበ ብርሃኔ እና ናትናኤል ግርማቸው**

አረ እንዴት ነሽ አረ እንዴት ነሽ (4)

የምን ሳቅ ጨዋታ ደግ ተሸኝቶ

ቀዬውም መንደሩም ተክዞ ሰንብቶ

የተፈጥሮ ነገር የውበትም ነገር

አንቺን ናፍቆ መዋል አንቺን ናፍቆ ማደር

አረ እንዴት ነሽ አረ እንዴት ነሽ(4)

ደስ አለኝ እመጣለሁ ስትይ ሰምተዋል መሰለኝ

ደስ አለኝ ዘማመሩ ወፎቹ ዜማቸው ደስ አለኝ

እመጣለሁ ስትይ ሰምተዋል መሰለኝ ደስ አለኝ

ዘማመሩ ወፎቹ ዜማቸው ደስ አለኝ

የአበቦ ድምቀት አቤት ውበታቸው

ከደጃፌ ደርሰሽ እስክታስንቂያቸው

ድጉሳው ተነሳ እንጀራውን ትቶ

ሊቀስምሽ መሰለኝ መምጣትሽን ሰምቶ

አረ ፈኩ ፈኩ አበቦች ከመስኩ

ለመለሙ ወፎች ተሳሳሙ

ዘማመሩ ዜማቸው ደስ አለኝ

መምጣትሽን ሰምተዋል መሰለኝ

አፈረች ጀንበሯም አፈረች

አፈረች አይንሽን እያየች

እያየች ተመኘች ደጅ ተቀምጣ

አንቺ ስትመጪ ልትሞቅሽ ብትወጣ

**ትራክ** 2 **ዳዊት ፅጌ ‹‹ባየው ባየው››**

**ድርሰት፡- ቴዎድሮስ ካሳሁን**

ዓይንሽን ባየው ባየው አልሰለችህ አለኝ ባየው(2)

መልክሽን ባየው ባየው ባየው አልሰለችህ አለኝ ባየው(2)

እንዲህ ውብ ተፈጥሮን የታደለ ማነው

ዓይንሽን አልሰለችህ አለኝ ባየው

የገላሽን ማማር የሰራ አካልሽን

የዓይን አገላለጥሽ አሰባበርሽን

እንዲህ ውብ ተፈጥሮን የታደለ ማነው

ዓይንሽን አልሰለችህ አለኝ ባየው

ሆድዬ ተይ አውጊኝ ምሽቱ ሳይነጋ

ልቤ እንዲረጋጋ

አንቺዬ ከነጋማ ወዲያ ብራ ነው

ተይ አውጊኝ ገና ነው

ከነጋማ ወዲያ ፀሐይ ከደመቀ

ምንም ሳላወጋሽ ሎሊቱ ካለቀ

ኋላ ብትናፍቂኝ ተጠያቂው ማነው

አይንሽ ቀን ከሌት አልሰለችህ አለኝ ባየው

አዝ

ማየቱንስ ያያል ሁሉም እንደ ህልሙ

ያንቺ ግን ይለያል ብዙ ነው ትርጉሙ

ይሄን ውብ ተፈጥሮ የታደለ ማነው

አይንሽን አልሰለችህ አለኝ ባየው

አንቺዬ ፈገግታሽ የጠዋት ጮራ ነው

አለም የሚሞቀው

አንቺዬ የልቤን ለልቤ ልንገረው

እይታሽ ፈራጅ ነው

ባይኖችሽ ብርሃን ድንቅ ውብ ፈገታሽ

የዘላለም ፍቅሩን አሜን ነው የሚልሽ

ይህን ታላቅ ውበት የተረዳው ማነው

ዓይንሽን ቀን ከሌት አልሰለችህ አለኝ ባየው

ባየው ባየው ባየው አልሰለችህ አለኝ ባየው

**ትራክ** 3 **ዳዊት ፅጌ ‹‹እትቴ››**

**ድርሰት፦ናትናኤል ግርማቸው**

እትቴ

እትቴ በረደኝ በቀን በጸሀይ

ናፍቆትሽ ክረምቱን ይዞት ገባ ወይ

ዛሬስ ዛሬስ ከዐይኔ ባጣሽ

ዛሬስ ድንገት በማርፈድሽ

ዛሬስ ሻንጣዬን አንስቼ

ወጣሁ ወጣሁ ልፈልግሽ

እትቴ በረደኝ በቀን በጸሀይ

ናፍቆትሽ ክረምቱን ይዞት ገባ ወይ

ዛሬስ ልፍስፍስ አልኩኝ ባንቺ

ዛሬስ ሰውነቴም ከዳኝ

ዛሬስ በልቤ ያለ ነገር

በሰው በሰው አፍ ላይዳኝ

ዛሬስ በሰው አፍ ላይዳኝ

በቀን መብራት ይገፍ ተቆጠርኩ እንደጅል

እኔስ ባንቺ ጉዳይ ድፍረትን አልከጅል

ሳልምሽ አምሽቼ ሲናፍቅሽ ዓይኔ

አንቺን ካለገኘሁ መንጋቱስ ለምኔ

የጫወታሽ ማማር የሳቅሽ ፏፏቴ

ውሃውን አስረሳኝ ሲፈስ ወደ አንጀቴ

ወንዙ ዳር አትገኝ መልክሽ ይታየኛል

አንቺን አሳቅቆ እኔን ይወስደኛል 2x

በወግ ያልነኩት ዘራፍ ሲሊት ሸሽቶ

ይታገለኝ ጀመር ፍቅርሽ ጦር አንስቶ

እንቺኑ ከሌለሽ ዝንጉን ይመልሰው

ጦር ይሠበቃል ወይ ጋሻ በሌለው ሰው 4x